የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAGF 06.10/1/24
ቀን 15/7/2014

ለጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ

ጂግጂጋ

ጉዳዩ፡- የጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፤ 42 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እና 12 ገጽ አባሪ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን። በመሆኑም በገጽ 64 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች አተገባበር መርሃ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ወርቅአፈራሁ ወንድሙ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

1. በዩኒቨርሲቲው በ2013 በጀት ዓመት ለኮቪድ -19 በልዩ ሁኔታ በጀት ተበጅቶ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000335244088 ብር 11,250,000.00 ገቢ የተደረገ ሲሆን ከዚህ መካከል ለተለያዩ ወጪዎች ብር 1,540,200.00 ክፍያ የተከፈለ ሲሆን ከወጪ ቀሪው ብር 9,524,421.20 ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ መደረግ ሲገባው ሰኔ 30/2013 ከወጪ ቀሪ ሆኖ የተመለከተ በመሆኑ አለአግባብ የባንክ ሂሳብ ክፍ እንዲል አድርጎታል፡፡
2. ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ሄደው ለሚማሩ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ግማሽ ደሞወዝ መከፈል ሲገባው ያለአግባብ ከመመሪያ ውጭ ሙሉ የወር ደመወዝ የተከፈለ በመሆኑ በድምሩ ብር 122,166.00 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፣
3. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር በቀን 06/01/2006 በቁጥርመ/90-1013/2 ለትምህርት ሚኒስቴር በተፃፈ ደብዳቤ ለከፍተኛ ትምህርት የአመራር አካላትና የአካዳሚክ

ባለሙያዎች ጥቅማ ጥቅምን በተመለከተ ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት መኖሪያ ቤት የማይሰጥ ከሆነ የቤት አበል በተሻሻለው የክፍያ ተመን መሰረት መከፈል እንዳለበት የተገለፀ ሲሆን የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸዉ የአመራር አካላትና ባለሙያዎች የቤት አበል ብር 57,600.00 የተከፈለ በመሆኑ መንግስት ተጨማሪ ወጪ እንዲከፍል አድርጎታል፡፡

4. የትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በሃገር ውስጥ በድህረ ምረቃ ለሚሰለጥኑ የዩኒቨርሲቲ መምህራን የሚሰጥ ድጋፍን በተመለከተ ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት መምህራኑ ከሚሰሩበት ዩኒቨርሲቲ ተንቀሳቅሰው ሀገር ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ ዩኒቨርሲቲ የሄዱ ሶስቱንም ድጋፎች (የቤት ኪራይ፣ ለፅህፈትና ለትራንስፖርት) ያገኛሉ፡፡ በሚሰሩበት ዩኒቨርሲቲ የሚሰለጥኑ ከቤት ኪራይ ድጋፍ በስተቀር ሌሎች የድጋፍ ዓይነቶችን እንደሚያገኙ የተገለጸ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ውስጥ እየሰሩ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ውስጥ ለሚሰለጥኑ ለ57 መምህራን የቤት ኪራይ ድጋፍ ተቀንሶ ክፍያ መፈፀም ሲገባ በድምሩ ብር 478,800.00 አላግባብ የቤት ኪራይ ድጋፍ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

5. ዩኒቨርሲቲው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ላይ ለተሳተፉ፣ ከኮሮና ወረርሽኝ ጋር ተያይዞ ግንዛቤ ለመፈጠር፣ በተለያዩ ቦታ የሚገኙ የርቀት ት/ት ማዕከላትን ዝግጅት ስራዎችን የሚቃኝ እና ለመከላከያ ሰራዊት ላበረከቱት አስተዋፆ የድጋፍ ፕሮግራም ላይ ለተሳተፉ ከተለያዩ የሚዲያ ተቋማት ለመጡ ጋዜጠኞች ከመጡበት ተቋም የደመወዛቸውን መጠን እና አበል ያልተከፈላቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ እንዲሁም ባለሙያዎቹ ከዩኒቨርሲቲው ጋር በምን ዓይነት የውል ስምምነት እንደመጡ ባልተገለጸበት ሁኔታ በድምሩ ብር 1,226,811.20 የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ የወጪዉን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም::

6. ዩኒቨርሲቲው የዕቃ ግዢ ለመፈጸም ከተለያዩ አቅራቢዎች ጋር በገባው የግዢ ስምምነት መሠረት አቅራቢዎቹ ከውል ስምምነቱ ውጭ ላዘገዩበት የጉዳት ካሳ በድምሩ ብር 919,634.60 ከአቅራቢዎች የግዢ ክፍያ ላይ መቀነስ ሲኖርበት ያልተቀነሰ (ያልተሰበሰበ) በመሆኑ መንግስት ማግኘት የሚገባውን ገቢ ያሳጣው መሆኑ፣

7. በሲኒላ ንግድ ድርጅት እና በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ መካከል በነበረው የአፈጻጸም የፌድራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከኢንተርፕራይዙ ለሲኒላ ንግድ ድርጅት በባንክ ካለው ሂሳብ ብር 609,800.00 እንዲታገድ ፍርድ ቤት የወሰነ ሲሆን እዳው ቢዝነስ ኢንተርፕራይዙ መክፈል ወይም ዩኒቨርሲቲው በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው

ከዩኒቨርሲቲ ሂሳብ የተቀነስና ሂሳቡ በወጪ የተመዘገበ በመሆኑ ያልተገባ የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል አድርጎታል፣

8. ዩኒቨርሲቲው በተለያየ ጊዜያት Organization mission& Vision፣ Leadership and Management change እና ስለ ጄኔሬተር አጠቃቀም ለአሰልጣኝና ለሰልጣኝ አስተባባሪዎች በሰዓት ብር 100 እና 120 በማሰብ የመምህራን እጥረት በሚታይባቸው የትምህርት ክፍሎች ክፍያ እንዲፈጸምበት በተፈቀደ የክፍያ ተመን ለስልጠና በድምሩ ብር 530,360.00 ከመመሪያ ዉጪ በመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተመን ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

9. ለዩኒቨርሲቲው በ2013 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች
   - ከመደበኛ በጀት ብር 18,172,915.10
   - ከካፒታል በጀት ብር 2,488,781.86
   - ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 1,796,319.03 በድምሩ ብር 22,458,015.99 በበጀት አርእስቱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ፤

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

1. <u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>

1.1. በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ በሳጥን የሚያዝ ጥሬ ገንዘብ በደንብና መመርያው መሰረት ብር 100,000.00 መሆን ሲገባው ሰኔ 30/2013 በውስጥ ኦዲት በሳጥን ተገኝቶ የተቆጠረው እና ለገንዘብ ሚኒስቴር በፈሰሰ ሪፖርት የተደረገው ጥሬ ገንዘብና ሰነድ ብር 439,592.09 መሆኑ፣

1.2. በዋናው ግቢ ብር 5,006,645.47 የግዥ ፍላጎትን አሰባስቦ በግልፅ ጨረታ ከመግዛት ይልቅ በርካታ ግዥዎችን ቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተፈጸመ በመሆኑ መንግስት ከውድድር ሊያገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያሳጣዋል።

1.3. **በዋና ግቢ ከሰንላይት መጸሐፍት መደብር** ከተገዛው መፅሃፍት ብር 682,630.00 መካከል የብር **158,890.00** የተከፈለ 27 ዓይነት መጻሀፍት ግዥ ከተሰጠው የጨረታ ትዕዛዝ የዕቃ ዝርዝር (specification) በውል ውስጥ ያልተካቱ ስሆን አቅራቢው አካል በተለያዩ የግል ችግር በመጥቀስ ቅሬታ ለዩኒቨርሲቲው በማቅረብ ውል የገቢ እንዲሆኑ ከተጠቀሱት መጽሀፍት ወጭ አቅራቢው መጽሀፍቶቹ ገቢ እንዲደረጉለት ብቻ ስለጠየቀ በሚል ብዛት 84 የሆኑ መጻሀፍቶች ከዩኒቨርሲቲ ፍላጎትና ውል ውጪ ወደ ግምጃ ቤት ገቢ የተደረገው በመሆኑ ብር **158,890.00** ያለአግባብ ወጪ እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡

1.4. **<u>አፈፃፀማቸው ደካማ የሆኑና የዘገዩ ግንባታዎች፣</u>**

- ይልማ ስራ ተቋራጭ በብር 73,233,158.05 እየተገነባ ያለው የዋና መግቢያ በር ግንባታ (Lot C-26) በቀን 04/08/2021 ዓ.ም ስራው የተጀመረ ሲሆን በ03/08/2021 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ የተገለጸ ቢሆንም እስከ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 43.5% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- በሳህለ ማሪያም ዘርጋው ህንጻ ስራ ተቋራጭ በብር 83,538,210.53 የሚገነባው ባለአራት ፎቅ የኮምፒውተር ማዕከል ስራ በ29/12/2017 የተጀመረ ሲሆን ግንባታው በ19/02/2020 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ የተገለጸ ቢሆንም እሰከ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) 48% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- ፋራጅ ኮንስትራክሽን በብር 5,162,646.07 ሲሚናር ህንጻ የጥገና ሥራ 24/07/2020 ዓ.ም የተጀመረው ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው 20/01/2020 ዓ.ም ቢሆንም እሰከ ሰኔ 30/2012 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 72% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- በማክሊን ቃሲም ህንጻ ስራ ተቋራጭ በብር 20,665,585.91 የሚገነባው ስቶር ህንጻና ሳይት ስራ በ09/12/2020 ዓ.ም በተገባ ውል ግንባታው የተጀመረ ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው በ09/12/2021 በጀት አመት መጨረሻ መጠናቀቅ ያለበት ቢሆንም እሰከ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 63.84% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ኢንተርፕራይዝ በብር 9,925,506.68 የሚገነባው የውሀና ፍሳሽ በይ 09/03/2020 ዓ.ም በተገባ ውል ግንባታው የተጀመረ ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው መጋቢት 2021 በጀት አመት መጨረሻ መጠናቀቅ ያለበት ቢሆንም እሰከ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 48% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤

- ቢዮሎ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ በብር 21,889,130.02 የሚገነባው የተሸከርካሪ ጋራጅና ፓረኪንግ አገልግሎት በ19/02/2020 ዓ.ም በተገባ ውል ግንባታው የተጀመረው ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው በ19/02/2021 ዓ.ም ቢሆንም እስከ ሰኔ 30/2012 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 0% ወይም ስራው ምንም ያልተጀመረ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- እስካ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ በብር 2,374,699.24 የሚገነባው እስፔሻላይዜሽን ህንጻ በ26/05/2021 ዓ.ም በተገባ ውል ግንባታው የተጀመረው ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው በ26/08/2121 ዓ.ም ቢሆንም እስከ ሰኔ 30/2012 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 0% የሚገኝ መሆኑ፤

1.5. በድምሩ ብር **421,584,874.70** በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

1.6. በድምሩ ብር 3,613,428.24 ሂሳቡ በወቅቱ ያልተወራረደ ተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፣

1.7. ለዩኒቨርሲቲው በ2013 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 39,799,202.26፣ ከካፒታል በጀት ብር 12,127,728.42 እና ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 16,193,658.32 በድምሩ ብር 68,120,589.00 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

2. <u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

2.1. የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፤ አያያዝ እና አጠባበቅ በፌደራል መንግስት ግዢና ንብረት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- <u>**የዩኒቨርሲቲዉ በተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት በተመለከተ**</u>

  - በዩኒቨርሲቲው አሮጌ ተመላሽ ስቶር ውስጥ ብዛት ያላቸው የተለያዩ ኤሌክትሮኒክሶች ሞኒተር ብዛት 109፣ ፕሮጀክተር ብዛት 18፣ ዩፒስ ብዛት 18፣ ፋክስ ብዛት 2፣ ሲፐዩ ዴል ኮር i2&i3 ብዛት 14፣ ፕሪንተር ብዛት 29፤ ፎቶ ኮፒ ብዛት 3፣ ኦቨን ብዛት 1፣ ኤር ኮንዲሽነር ብዛት 1፣ ውሃ ማሞቂያ ብዛት3፣ ቬንትሬተር ብዛት2፣ ሆል ማይክሮፎን ብዛት20፣ ኤሲ ሬጉሌተር ብዛት 55፣ ቲቪ ብዛት3፣ ላፕቶፕ ብዛት 23፣ ፋይል ካቢኔት ብዛት 2 እና የመኪና ጎማ ብዛት 6 ጨምሮ የሚሰሩና የማይሰሩ ሳይለዩና መወገድ የነበረባቸው ሳይወገዱ በአንድ ላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

❖ <u>የተማሪዎች ምግብ ቤት በተመለከተ</u>

- እለት ከእለት ወደ ተማሪዎች ምግብ ቤት ገቢ ሚደረግ እንጀራ ገቢ በሚሆንበት ወቅት የጥራት ኮሚቴና የተማሪዎች ህብረት ተወካይ በቦታ ተገኝቶ ጥራቱን የማያረጋግጥ መሆኑን በአካል ለማየት የቻልን መሆኑ
- እንደዚሁ እንጀራ በየእለቱ አቅራቢው ከተማሪዎች ቁጠርና በተቀመጠው የምግብ ሜኑ ተመጣጥኖ መቅረብ ሲገባው በዘፈቀደ የሚቀረብ መሆኑን
- ለዳቦ ማሽን አገልግሎት መንግስት በውድ ዋጋ ዳቦ እንዲሰራበት የተገዛ ማሽን ለበርካታ አመታት ያለ አገልግሎት ቤት ተዘግቶበት የተቀመጠ መሆኑን
- በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ምግብ ቤት ስቶር ቢን ካርድ በወቅቱ የማይቀናነስ መሆኑ፣
- በ2012 በጀት ዓመት የተገዛ በርበሬ 2 ዓመት ያለፈው ሲሆን አሁንም ድረስ 350 ኩንታል በላይ በስቶር ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፣

❖ <u>የተማሪዎች መድኃኒት ስቶርን በተመለከተ</u>

- የተማሪዎች መድኃኒት ክፍል(ዲስፔንሳሪ) ቢን ካርደ የማይሠራ መሆኑ፤

❖ <u>ሪፌራል ሆስፒታል በተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት በተመለከተ</u>

- የተለያዩ ተመላሽ ዕቃዎች በርካታ የታካሚዎች አልጋዎች፤ ሞተሮች፤ ፒፒሲዎች፤ጀሪካኖች ተለይተው ሳይመዘገቡና በወቅቱ ሳይወገዱ ተበታትነው የተቀመጡ መሆኑ፤

❖ **የሪፌራል ሆስፒታል የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች በተመለከተ**

- ቁጥራቸው የሆነ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መደድኃኒቶች በውቅቱ ሳይወገዱ እስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ

❖ <u>የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም በተመለከተ</u>

- በጠቅላላው 9 ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ጌጅ መቁጠሪያው የማይሰራ መሆኑ፤
- በጠቅላላው 8 ተሽከርካሪዎች ኮድ 4 መሆን ሲገባ በኮድ 3 ታርጋ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ፤
- በጠቅላላው 1 ተሽከርካሪ ኖርማላይዜሽን /ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት/ ያልተሰራላት /የሌላት/ መሆኑ፤

- በጠቅላላ 4 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ በተለያዩ ወቅት ለግንባታ ምክንያት ለተለያዩ የስራ ተቋራጮች በዩኒቨርሲቲ በጀት የተገዛ ቢሆንም ኮድ 3 ወደ ኮድ 4 በዩኒቨርሲተው ያልዞሩ መሆኑ፤

በጠቅላላው 10 ተሽከርካሪዎች በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

2.2. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የዩኒቨርሲቲውን የ2010,2011 እና 2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ዩኒቨርሲቲው ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ዩኒቨርስቲዉ {presenter and, discussant in senior and fresh student meeting] ስብሰባ ለተሳተፉ በሚል ለ257 የአካዳሚክ ሰራተኞች አላግባብ በመማር ማስተማር የትርፍ ሰዓት/በክሬዲት ሀወር/ የተጣራ ብር **240,325.30**፣ ለአዲስ እና ነባር ተማሪዎች በማህበረሰብ ስልጠና ወቅት ዋና ኮሚቴ ሆነዉ ለተሳተፉ እና ድጋፍ ላደረጉ ለ83 የአስተዳደር ሰራተኞች አላግባብ በመማር ማስተማር የትርፍ ሰዓት/ክሬዲት ሀዉር/ የተጣራ ብር **250,368.35**፣ በጠቅላላ ድምር ብር **490,693.65** ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ
- **<u>በዋናው ግቢ</u>** ከተወከል ጠቅላላ ትራንስፖርት ድርጅት ጋር የተለያዩ የትምህርት ክፍል ተማሪዎችን ከጅግጅጋ ወደ ሀረር ሲሄዱ በቀን ብር 4,300.00 በወር 129,000 ከጅግጅጋ ወደ ድሬዳዋ ሲሄዱ በቀን ብር 5,160.00 በወር 154,000 እና የሪፈራል ሆስፒታል ደግሞ ከሆስፒታሉ ወደ ጅግጅጋ ከተማ ለማመላለስ በቀን ብር 2,667.00 በወር 80,000.00 ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ የላይበራሪ ሰራተኞችን ከዩኒቨርስቲው ወደ ጅግጅጋ ከተማ ለማመላለስ ውል ሳይገባ አገልግሎት መገኘቱን ይህም ሆኖ ሆስፒታሉ የገባውን ውል ርቀታቸው ተመሳሳይ ስለሆነ ከሆስፒታሉ ወደ ከተማ ከመጠቀም ይልቅ ከጅግጅጋ ወደ ሀረር እና ከጅግጅጋ ወደ ድሬዳዋ ለማመላለስ በተገባ ውል ተመን ክፍያ በመፈጸሙ አለአግባብ በብልጫ ብር 394,600.00 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፡፡

- በሀሰን የበሬ ሪፈራል ሆስፒታል ከታረቀኝ ነጋሽ የደረቅ ጭነት አገልግሎት ድርጅት ጋር የግቢ ሰራተኞቹን ለማመላለስ ከህዳር 12/2012 ጀምሮ በየወሩ ሰማንያ ሺህ/80,000/ ለመክፈል ዉል የገባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በቀን 23/3/2012 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 576803 ሆስፒታሉ ዉል ከተያዘበት ከህዳር 12 ቀን ጀምሮ ብር **50,666.37**= (80,000/30*19} ለድርጅቱ መክፈል ሲገባዉ አላግባብ ሙሉ የህዳርን ወር ብር 80,000 በመክፈል ብር **29,333.37**=(80,000/30*11} በብልጫ የተከፈለ መሆኑን፣ በጠቅላላ ድምር ብር **423,933.37** በዋናው ግቢ እና በሆስፒታል ለትራንስፖርት በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ
- በድምሩ ብር 314,670,825.82 ውል የተገባ ስድስት ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከተ.ቁ.1-4 የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሳይያዝ ብር 88,600,619.52፣ ከተ.ቀ.1-6 ለውላቸው የውል ማስከበሪያ ሳይያዝ ብር 31,467,082.58 ውል መገባቱን በድምሩ ብር 120,067,702.10 ተመጣጣኝ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እና የውል ማስከበሪያ ሳይያዝ ፕሮጀክቶች በተቋራጭ ስራ የተጀመሩ ቢሆንም በተቋራጮች መጥፋት እና ተቋራጮች አፈጻጸም ድክመት ምክንያት በአሁኑ ወቅት ፕሮጀክቶቹ መቋረጣቸውን ከነዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 21,225,396.49 በስራ ተመላሽ መደረጉን እና ቀሪው በድምሩ ብር **98,842,305.61** ከጉዳት ካሳ ውጭ ከተቋራጪ የሚፈለግ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳሰብን ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡

ወርቅአፈራሁ ወንድሙ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

መጋቢት 2014

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ
የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓለማ፤

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲውን የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የዐርድና ማህደር መ/ቤት

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የባንክና ጥሬ ገንዘብ ሂሳብ</u>

1.1. <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ</u>

1.1.1 <u>በሰኔ 30/2012 በሳጥን የተቀጠረ ጥሬ ገንዘብን ፣</u>

በቀን 30/07/2007 ቁጥር ክሂመ39/7/9 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ በሳጥን የሚያዝ ጥሬ ገንዘብ መጠንን ስለማሻሻል በመጣው ማሻሻያ መሰረት ብር 100,000 እንዲሆን በሰርኩላር መወሰኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ በሳጥን የሚያዝ ጥሬ ገንዘብ በደንብና መመርያው መሰረት ብር 100,000.00 መሆን ሲገባው ሰኔ 30/2013 በውስጥ ኦዲት በሳጥን ተገኝቶ የተቆጠረው እና ለገንዘብ ሚኒስትር በፊሰስ ሪፖርት የተደረገው ጥሬ ገንዘብና ሰነድ ብር 439,592.09 መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

1.1.2. <u>ሥጋት፣</u>

- የመንግስት ደንብና መመሪያን ተግባራዊ የማይደረግ ከሆነ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡
- የጥሬ ገንዘብ ጫና እንዲፈጠር ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.1.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

1.1.4. <u>የሥራ አመራር ምላሽ፣</u>

በዩኒቨርሲቲው በበጀት አመቱ መጨረሻ በሰኔ 30/2013 በውስጥ ኦዲት በተደረገው ቆጠራ በሳጥን መገኘት ከነበረበት የጥሬ ገንዘብ በላይ በቆጠራ መገኘቱ ተብሎ ለቀረበው በወቅቱ ባሉት የገንዘብ ያገሮች የተለያዩ የሰራተኞች ክፍያዎች እና አንዳንድ የባንክ አካውንት የሌላቸው (ያላወጡ) ሰራተኞች የደሞዝ ክፍያ ሲሆን

ይኸውም ተከፋይ ሂሳብ በቀጣይ ባሉት ቀናቶች ለሰራተኞች የሚፈጸም ክፍያ መሆኑን በወቅቱ ከውስጥ ኦዲት ባለሙያዎች ጋር መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በመሆኑም በቀጥይ ተመሳሳይ አይነት ሁኔታ እንዳይከሰትና በካዝና መቀመጥ ከሚገባው የጥሬ ገንዘብ በላይ ወደ ካዝና እንዳይመጣ ሁሉንም ክፍያዎች በሰራተኞች የባንክ ሂሳብ እንዲፈጸም አድርገን እየሰራን ሲሆን ይህንኑ አጠናክረን እንደምንቀጥል እንገልፃለን፡፡

1.2. <u>ብሎክ እና ፈሰስ ያልተደረገ የባንክ ሂሳብን በተመለከተ ፤</u>

1.2.1 <u>ግኝት</u>

በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በቁጥር ከሂመ-39/4/30 በቀን 30/09/09 የመንግስት የባንክ ሂሳቦችን በተመለከተ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ የተላለፈ የአፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 3 በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ተቋማት ብሎክ በሚደረጉ ሂሳቦች ላይ መደረግ ያለባቸው ተግባራት ውስጥ ባንኩ ብሎክ ያደረጋቸው ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረገው ሂሳብ ፈሰስ መሆኑን ከትትል ማድረግ እንዲሁም የ2013 በጀት ዓመት የሐምሌ ወር የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ ብሎክ የተደረገው ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገበትን የባንክ አድቫይስ አያይዘው ማቅረብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው በ2013 በጀት ዓመት ለኮቪድ -19 በልዩ ሁኔታ በጀት ተበጅቶ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000335244088 ብር 11,250,000.00 ገቢ የተደረገ ሲሆን ከዚህ መካከል ለተለያዩ ወጪዎች ብር 1,540,200.00 ክፍያ የተከፈለ ሲሆን ከወጪ ቀሪው ብር 9,524,421.20 ባንኩ ብሎክ አድርጎ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ማድረግ ሲገባ ሰኔ 30/2013 ከወጪ ቀሪ ሆኖ የተመለከተ መሆኑና ፈሰስ አለመደረጉ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

1.2.2. <u>ሥጋት፤</u>

ዩኒቨርሲቲው መመሪያ ከመጣሱም በተጨማሪ የተጠቀሰውን ገንዘብ በፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት አለማሳየቱ ተመላሽ መሆን የነበረበት ሂሳብ በዩኒቨርሲቲው እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

1.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን ለሚመለከተው መ/ቤት ፈሰስ በማድረግ

ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ ብሎክ በሚደረጉ የባንክ ሂሳቦች ላይ ዩኒቨርሲቲው በመመሪያው የተሰጠውን ተግባር መፈጸም ይኖርበታል፡፡

1.2.4 <u>የሥራ ክፍል ምላሽ፤</u>

የኮቪድ -19 ወረርሽን ለመከላከል ከገንዘብ ሚኒስቴር ለተላለፈው የበጀት ድጋፍ የተከፈተው የባንክ ሒሳብ ቁጥር መደቡ ‹ኤ› ሆኖ የተከፈተ በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ ላይ ብሎክ ሊሆን ያልቻለ ሲሆን፤ በወቅቱ አገልግሎቱ ቀጣይነት የነበረው በመሆኑ እና ለዚሁ ተግባር ክንውን ከተፈጸሙት የተለያዩ ክፍያዎች ጋር ተያያዥ የሆኑ የታክስ ክፍያዎች ከመደበኛው በጀት ጋር በአንድነት ተዳምረው ለታክስ ባለስልጣኑ መ/ቤቱ ገቢ የተደረጉ በመሆኑ በዚሁ ሳቢያ፤ ተጨማሪ የማጣራት ስራ ለማከናወን ጊዜ በማስፈለጉ እና እንዲሁም ወረርሽኙን ለመከላከል የተላለፈውን የበጀት ድጋፉ የወጪ ሂሳቦችን አስመልክቶ በዩኒቨርስቲው የውስጥ ኦዲት አማካኝነት በተለያዩ ጊዜአቶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርቶች ቀርበው ግንዛቤ ተይዞባቸዋል፡፡

ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በበጀት ዓመቱ በዕቅድ ለተያዙ ተግባራት ማከናወኛ ለወጪ መሸፈኛ የሚውል ከፊል የመደበኛ በጀትን በመጠቀም በኮቪድ 19 በማቆያነት የህክምና አገልግሎት ለሚሰጣቸው ህሙማን ለዋለው በጀት እና በቀጥታ ለወረርሽኑ መከላከያ ዘግይቶ ለተላለፈው የበጀት ድጋፍ ያለውን የበጀት ብልጫ አጠቃቀምን አስመልክቶ ልዩ የወጪ አፈጻጸም መመሪያ ይተላለፋል የሚል እሳቤ በመያዙ ምክንያት የተፈጠረ ሲሆን፤በቀጣይ የቀረበውን የኦዲት ግኝት መነሻ በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ የምንወስድ ይሆናል፡፡

2. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

2.1 <u>ደመወዝና ተዛማጅ ክፍያዎች</u>

2.1.1 <u>ለትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ለሄዱ መምህራን አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ</u>

2.1.1.1 <u>ግኝት</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የቀድሞ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በቁጥር መ19/ጠ49/2/56 ቀን 22 መስከረም 1993 በተጻፈ ደብዳቤ ለትምህርት ወይም ለስልጠና ከ1 ወር በላይ ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ ከጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት በቀን 22/09/09 ዓ.ም በቁጥር ጠ80.አጠ52/01/09

በተላለፈው መመሪያ መሰረት በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው እንደሚከፈል ብቻ ይገልፃል፡፡ በዚህም መሰረት ለትምህርት ከሀገር ውጭ የሄዱ ሰራተኞች በመመሪያው መሠረት ግማሽ ደመወዝ ብቻ ክፍያ ለመፈፀሙ ኦዲት ሲከናወን፡- ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ሄደው ለሚማሩ የዩኒቨርሲቲ መምህር ለአቶ ሻረማርኬ ጃማ በየወሩ የግማሽ ወር ደመወዝ ብቻ መከፈል ሲገባው ያለአግባብ ከመመሪያ ውጭ ሙሉ የወር ደመወዝ በመከፈሉ በብልጫ ብር (5,652.00*12 = 67,830.00) እና ለአቶ አብዲሰላም ማአሊን ብር (4,528.00*12= 54,336.00) በድምሩ ብር 122,166.00 የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.1.1.2 ሥጋት

ለግለሰቦች መከፈል ካለበት በላይ ክፍያ መፈፀሙ የመንግስት ገንዘብ ለግለሰብ ጥቅም እንዲውል እና አሰራሩም በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ የመንግስት ገንዘብ በይበልጥ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

2.1.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

በመመሪያው መሰረት ወደ ውጭ ሀገር ከአንድ ወር በላይ ለሚቆዩ ሰራተኞች ወይም መምህራን በመመሪያው መሰረት ሊከፈል የሚገባው ግማሽ ደመወዝ ብቻ የሚል በመሆኑ ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን እንደሚከፈል የማያካትት በመሆኑ ለግለሰቦቹ አላግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የስራ አመራሩ ወደ ውጪ የሚሄዱ መምህራንን በተመለከተ የሚመለከተው ክፍል ሁሉ በወቅቱ መረጃ እንዲደርሰው ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- መ/ር ሸርማርኬ ጃማ የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ ውጪ ሀገር ለትምህርት መሄዳቸውን የሚገልፅ ምንም አይነት ማስረጃ በበጀት ዓመቱ /በ2013/ ለሰው ሀብት ስራ አመራር መምሪያ ዳይሬክቶሬት ያልቀረበ መሆኑ እየገለፅን ትምህርት ላይ እንደሆኑ ባወቅንበት ወቅት ማለትም በ2014 የትምህርት ዘመን መምህሩ ጠርተን ዋስ እንዲያቀርቡና ከዩኒቨርስቲው ጋር ውል እንዲገቡ ያደረግን ሲሆን መምህሩ ውል ሞልተው ካስገቡበት ከመስከረም ወር 2014ዓ.ም ጀምሮ በደብዳቤ ቁጥር ጅጅዩ/የሰ/ሀ/አ/መ/ዳ/855/ በቀን

19/2/2014ዓ.ም በፃፍነው ደብዳቤ መሰረት መ/ር ሽርማርኬ ጃማ ደመወዛቸውን በግማሽ እንድከፈላቸው በሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ያሳወቅን በመሆኑ በዚሁ አግባብ ክትትል ከማድረግ ባሻገር ሁለቱም ዳይሬክቶሬቶች (የሰው ሃብት እንዲሁም የፋይናንስ ክፍል) ከመቸውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ በጋራ በመናበብ ለተፈጻሚነቱ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ላይ እንገኛለን፡፡

- መ/ር አብዱሰላም ማአሊን የድህረ-ምረቃ ትምህርታቸውን ለመከታተል ዩኒቨርስቲው ወደ ውጪ ሀገር የላካቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁንና መምህሩ ለትምህርት ውጪ ሀገር ሲሄዱ ደመወዛቸው ግማሽ እንዲከፈላቸው መመሪያው በሚያዘው መሰረት መ/ር አብዱሰላም ማአሊን በደብዳቤ ቁጥር ጅጅዩ/የሰ/ሀ/ል/ስ አ/መ/ዳ/ 04440 በቀን 19/04/2013 ዓ.ም በፃፍነው ደብዳቤ መሰረት ከመስከረም 4 ቀን 2013 ጀምሮ የመምህሩ ደመወዝ ግማሽ እንዲሆን ደብዳቤ በሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶረት ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ያሳወቅን ቢሆንም ከስራ ክፍሉ ለመረዳት እንደተቻለው የመምህራኑን የደመወዝ መክፈያ ፔይሮል በወቅቱ ያዘጋጅ የነበረው ሙያተኛ የተረከበውን ደብዳቤ ስራ ላይ ካለማዋሉ በተጨማሪ ሰነዶችን አደራጅቶ በመያዝ ለተተኪው ፈጻሚ ተደራሽ ባለመደረጉ ምክንያት የተከሰተ ሲሆን የቀረበውን የኦዲት ግኝት መነሻ በማድረግ ከያዝነው ወር /ታህሳስ 2014 ዓ.ም/ ጀምሮ ከመምህሩ ተከፋይ ወርሃዊ ደመወዝ ላይ እንዲቆረጥ በማድረግ የዕርምት እርምጃ የምንወስድ ይሆናል፡፡

2.1.2 የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን የቤት አበል ክፍያ

2.1.2.1 ግኝት

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት በቀን 06/01/2006 በቁጥርመ/90-1013/2 ለትምህርት ሚኒስቴር በተፃፈ ደብዳቤ ለከፍተኛ ትምህርት የአመራር አካላትና የአካዳሚክ ባለሙያዎች ጥቅማ ጥቅም ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት መኖሪያ ቤት የማይሰጥ ከሆነ የቤት አበል በተሻሻለው የክፍያ ተመን መሰረት መከፈል እንዳለበት የተገለፀ ሲሆን በዚህም መሰረት ቤት የተሰጣቸው የቤት አበል እንደማይከፈላቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ከጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክተር በቀረበ ማስረጃ የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው የአመራር አካላትም ሆኑ ባለሙያዎች

የተከፈለ የቤት አበል ብር 57,600.00 መኖሩ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ 1 ቀርቧል)

2.1.2.2 <u>ስጋት</u>

ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት ገንዘብ ለግለሰቦች መሰጠቱ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ይዳርጋል፡፡ መንግስት ማግኘት የነበረበትን ገቢ እንዳያገኝም ያደርጋል፡፡

2.1.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን የሚከፈለው የቤት አበል አሰራሩ በአስቸኳይ እንዲቆም ማድረግ ይገባል፡፡ አላግባብ የተከፈለውም የቤት አበል ተጣርቶ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.1.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን የቤት አበል ክፍያ ተከፍሏቸዋል ተብሎ የቀረበውን የኦዲት ግኝቱን በግብአትነት በመውሰድ ተያያዥ መነሻ የሰነድ መረጃዎችን በተገቢው ሁኔታ በማጣራት ለፋይናንስ ክፍሉ ከሚመለከተው የስራ ክፍል የቤት ኪራይ ክፍያ እንዲቋረጥ የተላለፈውን የክፍያ ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ በተደረገው የማጥራት ስራ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ሆኗል፤ ይህ በዚህ እንዳለ የመኖሪያ ቤት ተሰጥቷቸው ለነበሩ መምህራን ከደመወዛቸው ላይ ተቀናሽ ይደረግ ተብሎ የተላለፈውን እና ሌሎች ተዛማጅ ማስረጃን በአባሪነት በማቅረብ እንዲያያዙ ተደርጓል፡፡

2.1.3 <u>በሀገር ውስጥ በድህረ ምረቃ ለሚሰለጥኑ መምህራን የቤት ኪራይ ወጪ ክፍያን በተመለከተ፤</u>

2.1.3.1 <u>ግኝት</u>

የትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በሃገር ውስጥ በድህረ ምረቃ ለሚሰለጥኑ የዩኒቨርሲቲ መምህራን የሚሰጥ ድጋፍን በተመለከተ ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት መምህራኑ ከሚሰሩበት ዩኒቨርሲቲ ተንቀሳቅሰው ሀገር ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ ዩኒቨርሲቲ የሄዱ ሶስቱንም ድጋፎች (የቤት ኪራይ፤ ለዕሀፈትና ለትራንስፖርት) ያገኛሉ፡፡ በሚሰሩበት ዩኒቨርሲቲ የሚሰለጥኑ ከቤት ኪራይ ድጋፍ በስተቀር ሌሎች የድጋፍ ዓይነቶችን እንደሚያገኙ›› መመሪያው በግልጽ ቢያስቀምጥም፤ በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ እየሰሩ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ውስጥ

ለሚሰለጥኑ መምህራን የቤት ኪራይ ድጋፍ ተቀንሶ ክፍያ መፈፀም ሲገባ ለ57 መምህራን በድምሩ ብር 478,800.00 አላግባብ የቤት ኪራይ ድጋፍ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ **(ዝርዝሩም በአባሪ ቁጥር 2 ቀርቧል)**

2.1.3.2 <u>ስጋት</u>

የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡ ከመመሪያ ውጭ የሚከፈል ገንዘብ ዩኒቨርሲቲውን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

2.1.3.3 <u>ማሻሻያ ሃሳብ</u>

በዩኒቨርሲቲው ለሚሰለጥኑ መምህራን አላግባብ የሚከፈለው የቤት ኪራይ ድጋፍ አሰራሩ እንዲቆም እና አላግባብ የተከፈለውም የመንግስት ገንዘብ በቀረበው የኦዲት ማስታወሻ መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በደመወዝ ዝግጅት ወቅት አስፈላጊው ጥንቃቄ እንዲወሰድ እናሳስባለን፡፡

2.1.3.4 <u>የስራ አመራር ምላሽ</u>

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እየሰሩ፤ በዚሁ ምክንያት በድህረ ምረቃ ፕሮግራም /በ2ኛ ዲግሪ/ እንዲሰለጥኑ የትምህርት እድል ለተሰጣቸው መምህራን የቤት ኪራይ ወጪ ድጋፍ የተፈጸመላቸውን ክፍያ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በመወያየት ለተማሪዎቹ የተፈጸመው የቤት ኪራይ ክፍያ አሰራሩ እዲቋረጥ /ቀጣይነት እንዳይኖረው ከማድረግ በሻገር ለተፈጸመው ክፍያ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር ግንዛቤ እንዲያዝበት በማድረግ አላግባብ ተከፋይ የሆነውን የቤት ኪራይ ድጋፍ ከመምህራኖቹ ተቀናሽ እንዲሆን ተገቢውን እርምጃ የምንወስድ ሲሆን ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ሁኔታ እንዳይከሰት አስፈላጊውን ጥንቃቄ በመውሰድ የምንሰራ ይሆናል፡፡

2.1.4 <u>ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል በተመለከተ</u>

2.1.4.1 <u>ግኝት</u>

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 3/2012 አንቀፅ 9 ቁጥር 1 ማንኛዉም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ዉጭ ወደ ሌላ ሥራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የቀን ዉሎ አበል መጠየቂያ፤ መክፈያና መፍቀጃ ቅፆች ለጉዳዩ አግባብ ባለው ሠራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ እንዲሞሉ ይደረጋል፡፡ ይህም ማለት የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ዉጭ ወደ ሌላ ሥራ ቦታ ለስራ

ጉዳይ ሲላክ መገጣጠሚያ ደብዳቤ ስለስራ ሁኔታው፣ ቆይታ…ወዘተ የሚገልፅ መያዝ ይኖርበታል፡፡

- በዚህ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ዩኒቨርሲቲው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ላይ ለተሳተፉ ፣ ከኮሮና ወረርሽኝ ጋር ተያይዞ ግንዛቤ ለመፈጠር፣ በተለያዩ ቦታ የሚገኙ የርቀት ት/ት ማዕከላትን ዝግጅት ስራዎችን የሚቃኝ እና ለመከላከያ ሰራዊት ላበረከቱት አስተዋፆ የድጋፍ ፕሮግራም ላይ ለተሳተፉ የተለያዩ የሚዲያ ባለሙያዎች በሚል ከተለያዩ የሚዲያ ተቋማት ለመጡ ጋዜጠኞች ከመጡበት ተቋም የደመወዛቸውን መጠን እና አበል ያልተከፈላቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ እንዲሁም ባለሙያዎቹ ከዩኒቨርሲቲው ጋር በምን ዓይነት የውል ስምምነት እንደመጡ ባልተገለጸበት ሁኔታ በድምሩ ብር 1,226,811.20 ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ የወጪዉን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

(ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል)

ቀን	ቫውቸር ቁጥር	የክፍያው አይነት	የተከፈለው ድርጅት	የገንዘብ መጠን
30/03/13	868226	ውሎ አበል	EBC,Fana,Obn,Walta tv	154,448.00
30/03/13	868216	ውሎ አበል	Srtv,Rtntv,Nbd tv,Jtv	118,112.20
30/03/13	867404	ውሎ አበል	EBC,Fana,Obn,Walta tv	161,699.00
30/03/13	868457	ውሎ አበል	Moshe,Addistv,EBC,Fanatv,Obn,Walta	242,400.00
30/05/13	867626	ውሎ አበል	EBC,Fana,Obn,Walta tv	176,856.00
30/05/13	867628	ውሎ አበል	EBC,Fana,Obn,Walta፣Dire tv	203,616.00
30/06/13	867650	ውሎ አበል	EBC,Fana,Obn,Walta tv፣ Amhara tv	169,680.00
ድምር				1,226,811.20

2.1.4.2 <u>ሥጋት</u>

ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት ከመዳረጉም ባሻገር ከመመሪያ ውጪ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነትን ያመጣል፡፡ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

2.1.4.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

የመስክ ስራው አስፈላጊ የመሆኑን ያህል ለመስክ ስራው እቅድና ዝርዝር ፕሮግራም በማውጣት ለሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ በማድረግ በመንግስት ላይ ተጨማሪ ወጪ እንዳያስከትል ስራው በእቅድ መመራትና በመስክ ስራው

አስፈላጊነት ቅደም ተከተል እንዲከናውን በማድረግ ውጤትን ማእከል ያደረገ አሰራር መከተል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ውጤት አልባ የሆነ በዘልማድ የሚፈጸም የመስክ ስራ ስምሪት ተጠያቂነት እንደሚያስከትል ታውቆ ጥንቃቄ የተሞላበት የመስክ ስራ እንቅስቃሴ በማድረግ የመስክ ስራዎቹ በበላይ ሃላፊዎች ዕውቅና፣በቁጠባና በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜት እንዲከናወኑ እና ወጪው ከተጨባጭ ውጤት ጋር የተዛመደ ለመሆኑ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

2.1.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

እንደሚታወቀው ዩኒቨርሲቲያችን የመማር ማስተማር፤ ጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች የሚያከናውን ሲሆን የዳይሬክቶሬታችን ዋና ተልዕኮም የተቋሙን አበይት ክንውኖች በሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ ማድረግ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ እነዚህ ክንውኖች በሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ የዩኒቨርሲቲያችን ገጽታ ጎልቶ እንዲታይ የማድረግ ተግባር ስናከናውን ቆይተናል፡፡

በዚህም አግባብ ዩኒቨርሲቲያችን በሚፈጽማቸው አበይት ክንውኖች ወቅት የተለያዩ ሚዲያዎችን (የተለያዩ ሚዲያ አማራጮችን የምንጠራበትም ምክንያት አድማጭ ተመልካቾች የየራሳቸው ሚድያ አማራጮች ስላሏቸው ነው) በመጋበዝ እንዲሁም በሶማሌ ክልል አሁን ባለው አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ልማት ምክንያት ሚዲያዎቹ ለተለያዩ ስራዎች በሚመጡበት ወቅት ለዩኒቨርሲቲያችንም ትኩረት ሰጥተው ሲጎበኙ ለተጨማሪ ቀናት በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ይቆያሉ፡፡ ከዚህም አኳያ በቆይታቸው ወቅት ለውሎ የሚሆን ወጪ ስለሚያስፈልጋቸው የውሎ አበል ወጪ እንዲሸፈንላቸው አድርገናል፡፡ ሚዲያዎቹም የዜናና ፕሮግራም ሽፋን በመስጠት ዩኒቨርሲቲያችን የሚከውናቸው ስራዎች ጎልተው እንዲታዩ ተገልጋይ አካላትም ስለተቋማችን የተሻለ ግንዛቤ እና እውቀት እንዲያገኙ አድርገዋል፡፡

ሆኖም ግን ሚዲያዎች ሽፋን እንዲሰጡን ለማድረግ በሁሉም ወቅቶች ሳይሆን ሚዲያ እንደ ምርቃት ስነ-ስርዓት፤ ታላላቅ ኮንፍረንሶች እና የመሳሰሉት ሀገራዊና አለማቀፋዊ ሁነቶች ላይ ኦፊሻላዊ ደብዳቤ እየላክን ሚዲያ የምንጋብዝ ሲሆን ነገር ግን በተወሰነ ደረጃ የዚህ አይነት አሰራር የዳበረ ባለመሆኑ ለሁሉም ክንውኖች ሚዲያ ሽፋን ስንፈልግ በደብዳቤ የመጥራት አሰራር በወጥነት አልተተገበረም፡፡

ስለሆነም የተነሳውን የኦዲት ግኝት የምንገነዘበው ሆኖ ሳለ ከላይ በተዘረዘረው ምክንያት ለሁሉም ክንውኖች የሚዲያ ሙያተኞችን በደብዳቤ የመጥራት የአሰራር ክፍተት የነበረ መሆኑን ግንዛቤ እንዲያዝበት እየገለፅን በቀጣይ ወቅቶች ወጥነት ባለው ሁኔታ ሚዲያዎች በኦፊሻላዊ ደብዳቤ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ የመንግስትን የፋይናንስ ህግ መሰረት በማድረግ ገቢር የምናደርግ መሆኑን ከወዲሁ በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

2.2 <u>ለእቃና አገልግሎት ግዥ፣</u>

2.2.1 <u>ከዕቃ አቅራቢዎች ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ፤</u>

2.2.1.1 <u>ግኝት፤</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደው እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት ይኖርበታል፤ እንዲሁም አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ላዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን 10% መብለጥ እንዳሌለበት ተገልጿል፡፡ በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ፤

ዩኒቨርሲቲው የዕቃ ግዢ ለመፈጸም ከተለያዩ አቅራቢዎች ጋር በገባው የግዢ ስምምነት መሠረት አቅራቢዎቹ ከውል ስምምነቱ ውጭ ላዘገዩበት የጉዳት ካሳ

- **በዋና ግቢ** ከተለያዩ አቅራቢዎች ብር 867,160.60
- **በሪፈራል ሆስፒታል** ከካሊድ ሳህኔ የቤትና ቢሮ ዕቃ አቅራቢ ድርጅት ብር 52,474.0 በድምሩ ብር 919,634.60 ከአቅራቢዎች የግዢ ክፍያ ላይ መቀነስ ሲኖርበት ያልተቀነሰ (ያልተሰበሰበ) መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

(ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 3 ቀርቧል)

2.2.1.2 <u>ሥጋት፤</u>

በዩኒቨርሲቲው የተገዛው ዕቃ በወቅቱ ቀርቦ ለታለመለት አላማ ላይውል ይችላል፡፡

2.2.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው በውሉ መሰረት አቅራቢዎችን ላዘገዩበት ቅጣት ከአቅራቢዎች ሰብስቦ ገቢ አድርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.2.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16.27 በንዑስ አንቀጽ 16.27.4 በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እቃውን ባያስረክብ ከቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ የጉዳት ካሳ መክፈል እንዳለበትና ከጠቅላላ ውሉ 10% መብለጥ እንደሌለበት በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ሆኖም ግን በዩኒቨርሲቲያችን የውል ሰራተኛ ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩት ሰራተኛ ለቀው በመሄዳቸውን ይህን ጉዳይ በቅርበት የሚከታል ሰራተኛ ስላልነበረ የተከሰተ ክፍተት መሆኑን አምነን ተመሳሳይ ችግር ለወደፊት እንዳይከሰት ብቁ የውል ባለሞያ ቀጥረን ስራውን በቅርበት እንዲከታተል የምናደርግ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

2.2.2 <u>ከቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ሂሳብ መክፈል ሲገባው ያለአግባብ ከዩኒቨርሲቲ የተከፈለ ሂሳብ በተመለከተ፤</u>

2.2.2.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌደራል መንግስት ፋይናንስ አስተዳድር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል ሁለት አንቀፅ 6/1 የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ስር የሚገኘው የመንግስት ሀብት ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግስት አካል ለፀደቀ አላማ ብቻ መዋሉን እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን፣ ብቃትን እና ውጤታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈፀሙን የማረጋገጥ ሃላፊነት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡- በቀን 05/04/2013 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 232146 በሂሳብ መደብ 6216 በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ስም ወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ሲሆን ሂሳቡ በሲኒላ ንግድ ድርጅት እና በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ መካከል በነበረው አፈጻጸም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከኢንተርፕራይዙ ለሲኒላ ንግድ ድርጅት በባንክ ካለው ሂሳብ ብር 609,800.00 እንዲታገድ ክርክር ፍርድ ቤት የወሰነ ሲሆን እዳው ቢዝነስ ኢንተርፕራይዙ መክፈል ሲገባው ያአላግባብ ከዩኒቨርሲቲ ሂሳብ ተቀንሶ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

2.2.2.2 ሥጋት፤

የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.2.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ፤

የራሱ ገቢ ላለው ቢዝነስ ኢንተርፕራይዙ ከዩኒቨርሲቲ ክፍያ መፈፀሙ ተገቢ ባለመሆኑ በጠቅላለው ለተፈፀሙ ክፍያዎች የወጪ መተኪያ በማድረግ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሂሳብ ተመላሽ ተደርጎ እና ለሚመለከተው መ/ቤት ፈሰስ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈፀም ተገቢ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.2.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ሂሳቡ በወቅቱ በሲኒላ ንግድ ድርጅት እና በዩኒቨርሲቲው የቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ መካከል በነበረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤ የፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ኢንተርፕራይዙ በወቀቱ የባንክ ሂሰቡን አግዶ ክፍያውን ለድርጅቱ ለመክፈል የሚያስችል በባንክ ሂሳቡ ውስጥ በቂ ስንቅ የሌለው በመሆኑና ኢንተርፕራይዙ በዩኒቨርሲቲው ስር የሚገኝ /አካል በመሆኑ የተላለፈውን የፍርድ ውሳኔ/ ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ ባንኩ ከዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ላይ በቀጥታ ወጪ እንዲሆን በማድረግ ክፍያን የፈጸመ በመሆኑ ሊከሰት የቻለ ሲሆን፤ከዚህም ጋር ተያይዞ የተመለከተውን የሂሳብ ምዝገባ፤ የወጪ እርዕስት የማስተካከያ የሂሳብ ምዝገባ ስራ በማከናወን ኢንተርፕራይዙን በተሰብሳቢ የሂሳብ መደብ ቀይሮ መዝግቦ ለመያዝ የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት ተጠናቆ የተዘጋ እና ለሚመለከተው አካል የቀረበ በመሆኑ ማስተካያ ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑን ግንዛቤ እንዲያዝበት በአክብሮት እየጠየቅን ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ሥርዓት እንዳይፈጸም ተገቢ ጥንቃቄና ቅጥጥር በማድረግ የምንሰራ ይሆናል፡፡

2.2.3. በአንድ ላይ መፈጸመ እየተቻለ ግዥ ከፋፍሎ መግዛትን በተመለከተ፤

2.2.3.1 ግኝት፤

በፌድራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 33/2 እና ሰኔ 2002 በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀጽ 15/2 መሠረት

በአዋጁና በመመሪያው በተፈጸመው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ በአዋጁ አንቀጽ 33/4 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ አዋጁ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ሥርዓቶችን ለመሸሽ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን መከፋፈል እንደሌለባቸው እንዲሁም፣ በመመሪያው አንቀጽ 24/1 እና 24/4 መሠረት ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋቸው በመመሪያው በተጠቀሰው መሠረት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ መፈፀም እንደሚቻል ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የግዥ ፍላጎትን አሰባስቦ ከመግዛት ይልቅ በርካታ ግዥዎችን ቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ግዢ በድምሩ ብር 5,006,645.47 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ **(ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 4 ቀርቧል)**

2.2.3.2 <u>ሥጋት፣</u>

የግዥ ስርዓትን በጠበቀ መልኩ ግዥ አለማከነወን መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግና ደንብና መመሪያ ሊጣስ ይችላል፡፡

2.2.3.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ግዥን ቆራርጦ መግዛት የመንግስት ገንዘብን ለብክነት እና ለከፍተኛ ወጪ ስለሚዳርግ የየክፍሉን የግዥ ፍላጎት በማሰባሰብ ግዥ ቢፈጽም በርካታ ተሳተፊ ድርጅቶች በወድድር ስለሚቀርቡና ከዋጋም አኳያ ዝቅተኛ ዋጋ ሊቀርብ ስለሚችል የመንግስት ወጪ ሊቀንስ ይችላል፡፡

2.2.3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

በአባሪ 11 ስንጠረዥ በቀረበው መሰረት ብዙን ግዜ በዋጋ ማቅረቢያ ያደረግናቸው ግዥዎች አመታዊ የግዥ እቅድ ፍላጎት ስናሰባስብ በእቅዱ ላይ ያልገቡና ያልተካተቱ ከመሆናቸው ባሻገር የግዥዎቹ አጣዳፊነትና ከግዥው ባህሪና ከዋጋቸው ጣሪያ አንጻር በ2008 የተሻሻለው የግዥ መመሪያ መሰረት በማድረግ የፈጸምናቸው መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

ይህን ስናደርግ ዩኒቨርሲቲው እንደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ብዛት ያላቸውን ተማሪዎች ከማስተናገድና ከነበረው የአገራዊ አለመረጋጋት ስጋት በዩኒቨርሲቲያችንም እንዳይከሰትና ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዳይስተጓጎል ከነበረን ስጋት አንጻር አጣዳፊና አስቸኳይ ያልናቸውን ግዥዎች በዋጋ ማቅረቢያ መፈጸማችንን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በምንጠቀምበት ወቅት መመሪያው ባስቀመጠው የገንዘብ ጣሪያና የተወዳዳሪዎች ብዛት በመጋበዝ የተቋማችን ሃብት ለብክነትና ለምዝበራ እንዳይጋለጥ የበኩላችንን ጥረት እያደረግን መሆኑን እየገለጽን ለመጪው 2014 በጀት አመት የግዥ ፍላጎታችንን ከተጠቃሚ የስራ ክፍሎች በትኩረት አሰባስበን በርካታ ድርጅቶች በውድድሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን አመቻችተን በግልጽ ጨረታ ግዥዎችን ለመፈጸም ከፍተኛ ጥረት የምናደርግ መሆኑን እገለጽን ለወደፊት ተመሳሳይ ግድፈቶች እንዳይፈጠሩ ተገቢውን ጥንቃቄ የምናደርግ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

2.2.3.5 የኦዲተሩ አስተያየት

በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በምንጠቀምበት ወቅት መመሪያው ባስቀመጠው የገንዘብ ጣሪያና የተወዳዳሪዎች ብዛት በመጋበዝ የተቋማችን ሃብት ለብክነትና ለምዝበራ እንዳይጋለጥ የበኩላችንን ጥረት እያደረግን ነው ቢባልም በግኝቱ ላይ የተገለጹት ግገርዎች የገንዘብ ጣሪያውን ባለመንካት በተመሳሳይ ቀን ከተመሳሳይ አቅራቢ የተገዙ በመሆናቸው ምላሹ ተቀባይነት የለውም በመሆኑም በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት እርማት እንዲወሰድ እናሳስባለን፡፡

2.2.4 ለአሰልጣኝና አስተባባሪ አለአግባብ የተከፈለ ክፍያን ይመለከታል

2.2.4.1 ግኝት

በኢ.ፌ.ድ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በ20/07/2011 በቁጥር 56/2011 ስለ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመንግስት በጀት ለሚሸፈኑ ወጪዎች የክፍያ ተመን መመሪያ ቁጥር 56/2011 መመሪያ መጋቢት 2011 ዓ/ም ክፍል 2 ተራ ቁጥር ከ1 እስከ 5. የመምህራን ዕጥረት ባለባቸዉ የትምህርት መስኮች የተጋባዥ መምህራን በተባባሪ

ፕሮፌሰር እና ከዚያ በላይ ደረጃ የክፍያ የተመን መጠን አከፋፈል በሰዓት ብር 250.00 ይከፈል፤ ለረዳት ፕሮፌሰር ደረጃ በሰዓት ብር 200.00፤ሌክቸር ደረጃ በሰዓት ብር 165.00 ፤ ከመደበኛዉ ፕሮግራም ዉጭ በረፍት ጊዜያቸዉ በመንግሥት በጀት ይከፈላል ይላል፡፡ የሚንስተሮች ምክር ቤት ግንቦት 25 ቀን 2009 የፌደራል መንግስት የ2010 በጀት አመት የበጀት ሰነዶችን በመገምገም ባስተላለፈዉ ዉሳኔ፤ ስልጠና እና ስብሰባ በተመለከተ፤- ከዚህ በፊት የሚደረጉ ስልጠናዎችና ስብሰባዎች ያገኙትን ዉጤት በመገምገም አስፈላጊ የሆኑ ስልጠናዎችን እና ስብሰባዎችን በመለየት ስልጠናዉ እና ስብሰባዉን በማካሄድ ወጪን መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ ጊዜ የሚደረጉ ስልጠናዎች እና ስብሰባዎች በአነስተኛ ወጪ ማለትም ሻይ፣ ቡና እና ዉሀ የመሳሰሉትን በማቅረብ ብቻ እንዲከናወን ማድረግ እንዳለበት ተወስኗል፡፡ በዚሁ መሰረት ክፍያው ስለመፈጸሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ዩኒቨርሲቲው በተለያየ ጊዜያት በቀን30/01/ ሳጥን የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 868018 Organization mission& Vision አሰልጣኝ፤ ስልጠና አስተባባሪዎች ብር 159,400.00 የተከፈለ በቀን 30/02/2013 ሳጥን የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 868537 Leadership and Management change ለስልጠና አስተባባሪዎች ብር 185,480.00 የተከፈለ እና በቀን 30/12/2012 ሳጥን የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 868517 ስለ ጀኔሬተር አጠቃቀም ለስልጠና አስተባባሪዎች ብር 185,480.00 በድምሩ ብር 530,360.00 የመምህርን እጥረት በሚታይባቸው የትምህርት ክፍሎች ክፍያ እንዲፈጸምበት በተፈቀደ የክፍያ ተመን /ክሬዲት ሀዉር/100 እና 120 በማሰብ አላግባብ ከመመሪያ ዉጪ ለአሰልጣኝና፤ ስልጠና ላስተባበሩ ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.2.4.2 ስጋት

- መንግሥት ያወጣውን መመሪያ ተከትሎ ያለመፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በላይ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.2.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ

መንግስት ያወጣውን መመሪያ ተከትሎ መስራት ይገባዋል፡፡ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጠር ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.2.4.4 የስራ አመራር ምላሽ

ዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ በእቅድ ለማከናወን ከያዛቸው ዘርፈ ብዙ ተግባረት መካከል አንዱ በከተማው/በአካባቢው በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሰራተኞችን በሚፈለገው ደረጃ አወዳድሮ በሚፈለገው የስራ ገበታ ለማሰማራት ከገቢው ላይ ለማግኘት በእጅጉ የሙያተኛ ውስንነት የሚስተዋል በመሆኑ በስራ ላይ የሚገኙ ሰራተኞችን በስልጠና ክህሎታቸውን በማሳደግ ለሚሰጡት አገልግሎት ብቁና ውጤታም እንዲሆኑ በማድረግ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው፡፡

ስለሆነም ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ተዘጋጅግቶ በሚቀርብ የስልጠና ዝርዝር ሰነድ (Training Proposal) መሰረት ለስልጠና መሸፈኛ የሚውለውን በጀት በማስፈቀድ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ባሉ መምህራንና በሙያ ዘርፉ ብቃት ያላቸውን አሰልጣኝ መምህራኖችን ከሌሎች ተቋማት ጋብዞ በማምታት ስልጠናዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፤ ስለሆነም በዚሁ አብባብ ለአሰልጣኞች፤ ለአስተባባሪዎች እና ለሌሎች ፈጻሚዎች ማለትም ስልጠናዎቹ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ በተሳካ ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆን የተጣለባቸውን የስራ ሃላፊነት በአግባቡ ለተወጡ ሰራተኞች የዩኒቨርስቲው የስራ ኃላፊዎች ይህንን በመገንዘብ ባስተላለፉት የክፍያ ትዕዛዝ መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን ችሏል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ ለግንዛቤ ያህል የስልጠና ሠነዶች በአቫሪነት ቀርበው ተያይዘዋል፡፡ በቀጣይ የቀረበውን የኦዲት ምክረ ሃሳብ በግብአትነት በመውሰድ የፋይናንስ ህጉ ለመሰል የስልጠና ተግባራት ያስቀመጠውን መመሪያ በመከተል ስራ ላይ የምናውል ይሆናል፡፡

2.2.5 በውል ሳይካተት ገቢ የሆነ የመጽሐፍ ግዢ በተመለከተ፤

2.2.5.1 ግኝት

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በቁጥር 2/ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (specification) መሰረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መስጠቱን፤ በቁጥር 4/አስፈላጊ ሲሆን እቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የፅሁፍ

ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነሐሴ 25/2011 ዓ.ም የፌዴራል መንግስትን በጀት ዓመቱ የሚመደብላቸውን በጀት በመንግስት በጀት ለታለመለት አላማ ማስፈፀሚያ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ማዋል እንደሚገባቸው ተገልፆል፡፡ በዚሁ መሰረት ግዥ ስለመከናወኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ዩኒቨርሲቲው **በዋና ግቢ** በቀን 09/10/2013 በወጪ ማስመስከሪያ 227605 ሰንላይት መጸሐፍት መደብር ብር 682,630.00 መካከል የብር 158,890.00_የተከፈል 27 ዓይነት መጻህፍት ግዥ ከተሰጠው የጨረታ ትዕዛዝ የዕቃ ዝርዝር (specification) በውል ውስጥ ያልተካቱ ስሆን አቅራቢው አካል በተለያዩ የግል ችግር በመጥቀስ ቅሬታ ለዩኒቨርሲቲው በማቅረብ ውል የገቢ እንዲሆኑ ከተጠቀሱት መጽሀፍት ወጭ አቅራቢው መጽሀፍቶቹ ገቢ እንዲደረጉለት ብቻ ስለጠየቀ በሚል ብዛት 84 የሆኑ መጻህፍቶች ከዩኒቨርሲቲ ፍላጎትና ውል ውጪ ወደ ግምጃ ቤት ገቢ የተደረገው በመሆኑ ብር 158,890.00 ያለአግባብ ወጪ እንዲያወጣ ተደርጓል፡፡ **(ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 5 ቀርቧል፡፡)**

2.2.5.2 <u>ስጋት</u>

አስፈላጊነታቸው በመንግስት ታምኖበት የወጡ አዋጀች ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ እንዲሁም ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

2.2.5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት አይችልም፡፡ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ያለአግባብ የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡እንደሁም መ/ቤቱ ያስቀመጠው ውል ውጪ ገቢ እንዲሆን ያደረጉ አካላት አስፈላጊው የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

2.2.5.4 <u>የስራ አመራር ምላሽ</u>

- ከተጠየቁት 27 ዓይነት መፅሐፍቶች 26ቱን ዓይነት መፅሐፍት በዩኒቨርሲቲው የተቋቋመው ቴክኒካል ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት የተቀበለውን መፅሐፍት ብቻ ገቢ

ያደረግን መሆኑን የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ ኮፒ አድርገን አባሪ ያደረግን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

- ነገር ግን በአይነት አንድ እና በብዛት 11 የሆኑትን መፅሐፍት ኮሚቴው በ እስፔስፍኬሽን (Specification) መሰረት ስላልነበረ ገቢ አላደረግንም፡፡

3. የግንባታ ክፍያዎችን በተመለከተ

3.1 በጊዜ ገደባቸው ያልተጠናቀቁ የግንባታ ግብዓት ሂሳብ በተመለከተ

3.1.1 ግኝት

በግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስር 12 ዩኒቨርሲቲዎች በግንባታ ላይ ያሉ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠናቀው አገልግሎት ላይ ለመዋላቸው እና ሥራ ተቋራጮችም በገቡት ውል መሠረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የተገኙ ሁኔታዎች ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

- ይልማ ስራ ተቋራጭ በብር 73,233,158.05 እየተገነባ ያለው **የዋና መግቢያ በር ግንባታ** (Lot C-26) በቀን 04/08/2021 ዓ.ም ስራው የተጀመረ ሲሆን የሚጠናቀቀው 03/08/2021 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ የተገለጸ ቢሆንም ከግንባታ ክፍል በተሰጠን መረጃ መሰረት እስከ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 43.5% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- በሳህለ ማሪያም ዘርጋው ህንጻ ስራ ተቋራጭ በብር 83,538,210.53 የሚገነባው ባለአራት ፎቅ የኮምፒውተር ማዕከል ስራ በ29/12/2017 የተጀመረ ሲሆን ግንባታው በ19/02/2020 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ የተገለጸ ቢሆንም ከግንባታ ክፍል በተሰጠን መረጃ መሰረት እስከ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) 48% ላይ የሚገኝ መሆኑ
- ፋራጅ ኮንስተራክሽን በብር 5,162,646.07 ሲሚናረ ህንጻ የጥገና ሥራ 24/07/2020 ዓ.ም የተጀመረው ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው 20/01/2020 ዓ.ም ቢሆንም ከግንባታ ክፍል በተሰጠን መረጃ መሰረት እስከ ሰኔ 30/2012 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 72% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- በማክሊን ቃሲም ህንጻ ስራ ተቋራጭ በብር 20,665,585.91 የሚገነባው እስቶር ህንጻና ሳይት ስራ በ09/12/2020 ዓ.ም በተገባ ውል ግንባታው የተጀመረ ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው በ09/12/2021 በጀት አመት መጨረሻ መጠናቀቅ ያለበት

ቢሆንም ከግንባታ ክፍል በተሰጠን መረጃ መሰረት እስከ ሰኔ 30/2012 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 63.84% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤

- ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ እንተርፕራይዝ በብር 9,925,506.68 የሚገነባው የውሀና ፍሳሽ ቦይ 09/03/2020 ዓ.ም በተገባ ውል ግንባታው የተጀመረ ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው መጋቢት 2021 በጀት አመት መጨረሻ መጠናቀቅ ያለበት ቢሆንም ከግንባታ ክፍል በተሰጠን መረጃ መሰረት እስከ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 48% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- ቢዮሎ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ በብር 21,889,130.02 የሚገነባው የተሽከርካሪ ጋራጅና ፓረኪንግ አገልግሎት በ19/02/2020 ዓ.ም በተገባ ውል ግንባታው የተጀመረው ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው በ19/02/2021 ዓ.ም ቢሆንም ከግንባታ ክፍል በተሰጠን መረጃ መሰረት እስከ ሰኔ 30/2012 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 0% ወይም ስራው ምንም ያልተጀመረ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- እስካ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ በብር 2,374,699.24 የሚገነባው እስፔሻላይዜሽን ህንጻ በ26/05/2021 ዓ.ም በተገባ ውል ግንባታው የተጀመረው ሲሆን ስራው የሚጠናቀቀው በ26/08/2121 ዓ.ም ቢሆንም ከግንባታ ክፍል በተሰጠን መረጃ መሰረት እስከ ሰኔ 30/2012 ዓ.ም የግንባታው ደረጃ (Project status) ገና 0% የሚገኝ መሆኑ፤በኦዲት ወቅት በናሙና ካየናቸው ውስጥ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

3.1.2 ሥጋት

የግንባታ ስራዎች በተገባው ውል መሰረት በወቅቱ ካልተጠናቀቁ በታቀደው መሰረት በአሰሪው መ/ቤት አገልግሎት መስስጠት የማይችሉ ከመሆኑ ባሻገር ከግንባታ ዕቃዎች ጋር ዋጋ መጨመር አንጻር መንግስት ላልተፈለገ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

3.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

የግንባታ ስራዎች በተገባው ውል መሰረት እንዲጠናቀቁ ተገቢው ቁጥጥር ማድረግ፤ በተጨማሪም በገቡት ውለታ መሰረት ግዴታቸውን ባልተወጡ የስራ ተቋራጮች ላይ ተገቢው የጉዳት ካሳ እንዲከፈሉ ማድረግ ይገባል፡፡

3.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

የጊዜ ገደብን በተመለከተ ግንባታቸው መጠናቀቅ ከነበረበት ጊዜ በላይ የወሰደና ያልተጠናቀቁ ግንባታዎች በተመለከተ ከ2013 ዓ.ም በፊት የተጀመሩ በ2013 ዓ.ም መጠናቀቅ የነበረባቸው ነባር ፕሮጀክቶች የውል ጊዜው አለማለቁ (መጓተቱ) የነበሩ ተግዳሮቶች

- የግንባታ ግበአቶች መጥፋት
- የዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር
- ዩንቨርሲቲው በዋናው ግቢ የወሰን ማስከበር ስራ አለመሰራቱ ምክንያት ሊጓተቱ በመቻላቸው ተቋራጮቹ በክፍያ መዘግየት ምክንያት ዩንቨርሲቲው ሊቀጣ የሚችለውን ገንዘብ ታሳቢ ባደረገና ተቋራጮቹ ግንባታውን ጨርሶ ለማስረከብ ካለቸው ፍላጎት ጋር ወደ ተጨማሪ ጊዜ በመቀየር ስራውን እንዲሰሩ ለማድረግ የተሰራ ስራ ሲሆን ውሉ ቢቋረጥ መንግስት ላይ ሊያመጣ ከሚችለው የዋጋ ጭማሪ ላልተገባ ወጪ ይዳርግ ነበር።

4. በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

4.1 ግኝት፣

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ "ለ" የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ 7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበትና በንዑስ አንቀጽ "መ" ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ መመሪያው ቢያመለክትም ብር 421,584,874.70 በጊዜ ገደቡ መወራረድ ሲገባው ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝርም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የተሰብሳቢ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር

ተ.ቁ	የሂሳብ መደብ ቁጥር	የቆይታው ጊዜ			ድምር
		ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ	ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ	ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ድረስ የቆየ	
1	4201	20,991,412.43	33,063,765.80		54,055,178.23
2	4203		611,855.36	109,607.96	721,463.32
3	4210	540,000.00	27,785,985.52	253,128.27	28,579,113.79
4	4251	35,705,952.74	253,534,386.72		289,240,339.46
5	4253	12,750,000.00	30,044,655.58	700,350.00	43,495,005.58
6	4273	2,174,952.70	3,065,682.26		5,240,634.96
7	4274	181,285.00	71,854.36		253,139.36
ድምር		72,343,602.87	348,178,185.60	1063086.23	421,584,874.70

4.2 ሥጋት፣

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለው የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፣ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

➢ ዩኒቨርሲቲው ለተሰብሳቢ ሂሳቦች ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ሲሆን ይኸውም በሂሳብ መደብ 4201 በአብዛኛው ለመምህራን ለጥናትና ምርምር ስራዎች በስማቸው ወጪ ያደረጉት

ሂሳብ ሲሆን የበጀት አመቱን ጨምሮ ያለፉትን በጀት አመታት ሂሳብ ጨምሮ የሚታይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲው የዋና ግቢና የሪፈራር ሆስፒታል ጥምር ሂሳብ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ሂሳቦች የበጀት አመቱን ሳይጨምር ያለፉትን አመታት ሂሳቦች እንዲወራረድ ከጥናትና ምርምር ም/ፕሬዝዳንት ቢሮ ጋር በመሆን በጋር እየሰራን እንገኛለን፡፡ አንዳንድ መወራረድ የማችሉትን የለቀቁ መምህራን ጉዳይ ወደ ህግ አግባብ በመሄድ እንዲወራረድ በከፍተኛ ትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡

- ከዚህም በተጨማሪም የግንባታ እና የግዥ ቅድመ ክፍያዎችንም በሚመለከት ከሚመለከተው የዩኒቨርሲቲው አመራር ጋር በመገናኘት የግንባታዎ አፈፃፀም ጋር የተገናኘ በመሆኑ የክፍያ ማረጋገጫ ሲቀርብ የቅድመ ክፍያዎችም ተቀናሽ በማድረግ የሚወራረድ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- በአጠቃላይ የተሰብሳቢ ሂሳቦችን በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ እና በጉዳዩ ላይ ትኩረት በመስጠት ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር እየሰራ ሲሆን በቀጣይ በከፍተኛ ሁኔታ ተሰብሳቢ ሂሳብ ለመቀነስ እየሰራን እንገኛል፡፡

5. <u>በወቅቱ ያልተወራረደ የተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ፤</u>

5.1 <u>ግኝት</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ ሀ «ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት›› እና በንዑስ አንቀጽ ሐ ‹‹መ/ቤቶች ከተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብርና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለባቸው›› መመሪያው ቢያመለክትም፤ ዩኒቨርሲቲው ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የተከፋይ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር

ተ.ቁ	የሂሳብ መደብ ቁጥር	የቆይታው ጊዜ				ድምር
		ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ	ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ	ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት ድረስ የቆየ		
2	5021	199,278.50				199,278.50
3	5026		20,000.00			20,000.00
4	5028	170,542.33	3,223,607.41			3,394,149.74
ድምር		369,820.83	3,243,607.41			3,613,428.24

5.2 ስጋት፣

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

5.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የመጣውና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቀው ተከፋይ ሂሳብ ሁኔታም ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በ2013 በጀት አመት የሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታየው በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል በቀጣይ ባሉት ወራቶች የተከፈለ ሲሆን ይኸውም በዊዝሆልዲንግ እና በተጨማሪ እሴት ታክስ የበጀት አመቱን በሙሉ ለገቢዎች ባለስልጣን የተላለፈ ቢሆንም በበጀት አመቱን መጨረሻ በተፈፀሙ ክፍያዎች የተሰበሰበው በቀጣይ ባሉት ወራቶች ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ገቢ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከግንባታ ሂሳብ ላይ የተቀነሰ የተከፋይ ሂሳብ የግንባታ አፈፃፀም ጋር

የሚገናኝ ሲሆን ይኸውም ግንባታው ርክክብ ተደርጎ የክፍያ ሲቀርብ ተከፋይ የሚሆን ሂሳብ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሌሎችም ተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከተው አካል በቀጣይ በማስተላለፍ የሚወራረድ ይሆናል፡፡

6. <u>በጀት፣</u>

6.1 <u>የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ፣</u>

6.1.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡- ለዩኒቨርሲቲው ለ2013 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የመደበኛ በጀት፣ የውስጥ ገቢና የካፒታል በጀት ወጪ በሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ፡-

- ከመደበኛ በጀት ብር 39,799,202.26
- ከካፒታል በጀት ብር (50,133,681.16-38,005,952.74)=12,127,728.42
- ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 16,193,658.32

በድምሩ ብር **68,120,589.00** ሥራ ላይ ያልዋለና እንዲሁም ከመደበኛ በጀት ብር (26,480,819.98-8,307,904.88)= **18,172,915.10** ከካፒታል ብር 14,287,093.77(ከዚህ ውስጥ በባለፈው የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ የተወራረደ ብር 11,798,311.91 ሲሆን) ብር 2,488,781.86 እና ከውስጥ ገቢ ብር 1,796,319.03 በድምሩ ብር **22,458,015.99** ከተፈቀደ በጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡ **(ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)**

6.1.2 <u>ሥጋት፣</u>

የወጪ በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

6.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውን የተጣጣመ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ በ2013 በጀት አመት የተመደበለትን በጀት ለታለመለት አላማ በአግባቡ በመመሪያው መሰረት በአብዛናው ስራ ላይ ያዋለ ሲሆን በግኝት የተገለጸው ስራ ላይ ያልዋለ በጀት የተባለው በአንዳንድ የበጀት አርዕስት በተለይ በካፒታል በጀት በቅድመ ክፍያ የተፈፀመ ክፍያ ምዝገባው የሚመዘገበው በተሰብሳቢ ስለሆነ እና በወጪው ላይ ስለማይታይ ተሰብሳቢው ጨምሮ ወጪው ይቀንሳል፡፡ ይህ ማለት በጀቱን ተጠቅመን ስራ ላይ የዋለ ቢሆንም በወጪ ስለማይታይ ጥቅም ላይ ያልዋለ በጀት ተብሎ መቅረብ የለበትም፡፡ ስለሆነም በዚህ ላይ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ሆኖም ግን በአንዳንድ የበጀት አርዕስቶች የተወሰነ ጥቅም ላይ ሳይውል የቀረ በጀት ይኖራል፡፡ ሌላው ከበጀት በላይ አጠቃቀም ተብሎ የቀረበው ይህም ካለፉት የበጀት አመታት በተሰብሳቢ ተመዝግበው የነበሩ ሂሳቦች በበጀት አመቱ በመወራረዳቸው በሂሳብ መደቦቹ ወጪው እንዲጨምር አድርጎታል፡፡ በአብዛኛው የተከሰተው በዚህ አይነት ሁኔታ ቢሆንም በአንዳንድ ሂሳብ ምድቦች በተወሰነ መልኩ ከበጀት በላይ አጠቃቀም ሊታይ ችሏል፡፡ በአጠቃልይ ከላይ በተገፀው መሰረት የበጀት አጠቃቀም ግንዛቤ እንዲወሰድበት እየጠየቅን ለወደፊቱ ተመሳሳይ አይነት ሁኔታ እንዳይከሰት በጥንቃቄ እንደምንሰራ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

7 <u>ንብረት</u>

7.1 <u>በንብረት አያያዝ ላይ የታዩ ክፍተቶችን በተመለከተ፤</u>

7.1.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል አራት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ከሀ-ሰ ስለመንግስት ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ ምዝገባ በሚለው ስር ‹‹የመንግሥት መ/ቤት በግዥ፣በስጦታ፣በዝውውር...ወዘተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ

የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ ቢያንስ የሚከተሉት መረጃዎች መዝግቦ ይይዛል፤ የተሽከርካሪውን አይነትና ሞዴል፣ የጭነቱ ልክ (በሰው፣ በኩንታል፣ በኪዩቢክ ሜትር ወይም በሊትር ተለይቶ)፤ የቻንሲና የሞተር ቁጥሮች፣ የሚጠቀመው የነዳጅ አይነት፤ የተገዛበት ወይም በመ/ቤቱ ባለቤትነት ሥር የዋለበት ቀንና ዓመተ ምህረት፤ የተሽከርካሪው ዋጋ እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ቁጥር›› መያዝ እንዳለበት መመሪያው ቢያመለክትም፤የዩኒቨርሲቲው የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በዋና ግቢ

- **የዩኒቨርሲቲዉ በተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት በተመለከተ**
  - በዩኒቨርሲቲው አሮጌ ተመላሽ ስቶር ውስጥ ብዛት ያላቸው የተለያዩ ኤሌክትሮኒክሶች ሞኒተር ብዛት 109፣ ፕሮጀክተር ብዛት 18፣ ዩፒስ ብዛት 18፣ ፋክስ ብዛት 2፣ ሲፒዩ ዴል ኮር i2&i3 ብዛት 14፣ ፕሪንተር ብዛት 29፤ ፎቶ ኮፒ ብዛት 3፣ ኦቨን ብዛት 1፣ ኤር ኮንዲሽነር ብዛት 1፣ ውሃ ማሞቂያ ብዛት3፣ ቬንትሬተር ብዛት2፣ ሆል ማይክሮፎን ብዛት20፣ ኤሲ ሬጉሌተር ብዛት 55፣ ቲቨ ብዛት3፣ ላፕቶፕ ብዛት 23፣ ፋይል ካቢኔት ብዛት 2 እና የመኪና ጎማ ብዛት 6 ጨምሮ የሚሰሩና የማይሰሩ ሳይለዩና መወገድ የነበረባቸው ሳይወገዱ በአንድ ላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- **የተማሪዎች ምግብ ቤት በተመለከተ**
  - እለት ከእልት ወደ ተማሪዎች ምግብ ቤት ገቢ ሚደረግ እንጀራ ገቢ በሚሆንበት ወቅት የጥራት ኮሚቴና የተማሪዎች ህብረት ተወካይ በቦታ ተገኝቶ ጥራቱን የማያረጋግጥ መሆኑን በአካል ለማየት የቻልን መሆኑ
  - እንደዚሁ እንጀራ በየእለቱ አቅራቢው ከተማሪዎች ቁጠርና በተቀመጠው የምግብ ሜኑ ተመጣጥኖ መቅረብ ሲገባው በዘፈቀደ የሚቀረብ መሆኑን
  - ለዳቦ ማሽን አገልግሎት መንግስት በውድ ዋጋ ዳቦ እንዲሰራበት የተገዛ ማሽን ለበርካታ አመታት ያለ አገልግሎት ቤት ተዘግቶበት የተቀመጠ መሆኑን

- በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ምግብ ቤት ስቶር ቢን ካርድ በወቅቱ የማይቀናነስ መሆኑ፣
- በ2012 በጀት ዓመት የተገዛ በርበሬ 2 ዓመት ያለፈው ሲሆን አሁንም ድረስ 350 ኩንታል በላይ በስቶር ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፣

❖ **የተማሪዎች መድኃኒት ስቶርን በተመለከተ**

- የተማሪዎች መድኃኒት ክፍል(ዲስፔንሳሪ) ቢን ካርደ የማይሠራ መሆኑ፤

❖ **<u>ሪፈራል ሆስፒታል በተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት በተመለከተ</u>**

- የተለያዩ ተመላሽ ዕቃዎች በርካታ የታካሚዎች አልጋዎች፤ ሞተሮች፤ ፒፒሲዎች፤ጀሪካኖች ተለይተው ሳይመዘገቡና በወቅቱ ሳይወገዱ ተበታትነው የተቀመጡ መሆኑ፤

❖ **የሪፈራል ሆስፒታል የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች በተመለከተ**

- ቁጥራቸው የሆነ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መደድኃኒቶች በወቅቱ ሳይወገዱ እስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ

❖ **<u>የተሽከረካሪ አያያዝና አጠቃቀም በተመለከተ</u>**

- በጠቅላላው 9 ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ጌጅ መቁጠሪያው የማይሰራ መሆኑ፤
- በጠቅላላው 8 ተሽከርካሪዎች በኮድ 3 ታርጋ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ፤
- በጠቅላላው 1 ተሽከርካሪ ኖርማላይዜሽን /ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት/ ያልተሰራላት /የሌላት/ መሆኑ፤
- በጠቅላላ 4 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ በተለያዩ ወቅት ለግንባታ ምክንያት ለተለያዩ የስራ ተቋራጮች በዩኒቨርሲቲ በጀት የተገዛ ቢሆንም ኮድ 3 ወደ ኮድ 4 በዩኒቨርሲተው ያልዞሩ መሆን፤
- በጠቅላላው 10 ተሽከርካሪዎች በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ (ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ 7 ቀርቧል)

7.1.2 <u>ስጋት</u>

ዩኒቨርሲቲው መንግሥት ባወጣዉ የንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ፡-ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓት መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ የመንግሥት ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

7.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከልና እንዲፈጸም ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢው ሥራ መሰራት ይኖርበታል፡፡

7.1.4 የስራ አመራር ምላሽ

- ከተጠየቁት 27 ዓይነት መፅሐፍቶች 26 ቱን ዓይነት መፅሐፍት በዩኒቨርሲቲው የተቋቋመው ቴክኒካል ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት የተቀበለውን መፅሐፍት ብቻ ገቢ ያደረግን መሆኑን የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ ኮፒ አድርገን አባሪ ያደረግን መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ነገር ግን በአይነት አንድ እና በብዛት 11 የሆኑትን መፅሐፍት ኮሚቴው በ እስፔስፍኬሽን (Specification) መሰረት ስላልነበረ ገቢ አላደረግንም

በተማሪዎች ምግብ ግምጃ ቤት በተመለከተ

- የተማሪዎች ምግብ ግምጃ ቤት በየግዜው ቢንካርድ እንደሚሰራ ይታወቃል፡፡ ነገርግን በሰአቱ የተወሰኑ ምግቦች የመጨረሻሳምንት ወጭ የሆኑበት ስላልተቀናነሰ አሁን ግን ስለተቀናነሰ የቢን ካርድ ኮፒ አባሪ አድርገናል፡፡
- በ 2012 በጀት አመት የተገዛ በርበሬ በኮቪድ 19 መከሰት ምክንያት በተማሪዎች ለአንድ አመት አካባቢ ውስጥ ባለመኖራቸው ምክንያት 350 ኪስ በርበሬ ሊተርፍ ችሏል፡፡ ነገርግን አሁን ተማሪዎች በመግባታቸው ጋር ተያይዞ በሚቀጥሉት 4 ወራት ውስጥ ያልቃል፡፡
- የተማሪ እንጀራ አቅርቦት ጥራት ማረጋገጥን በተመለከተ የተማሪዎች ህብረት ንዑስ ካፌ ኮሚቴ አባላት እና የካፍቴሪያው ስራተኞች በጋራ በመሆን እለት- በዕለት ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና የክትትል ስራዎችን የሚሰሩ ሲሆን፣ ነገር ግን ሰሞኑን አብዛሃኞቹ የተማሪ ህብረት ተወካዮች ለዕረፍት ስለሄዱና በግቢው ውስጥ ያሉት በቁጥር አናሳ በመሆናቸው ወደ ክላስ በሚሄዱበት ሰአት አልፎ አልፎ ክፍተት ሊፈጠር ቢችልም የእንጀራ ጥራት ቁጥጥሩ በካፍቴሪያው ስራተኞች ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን

እረፍታቸውን አጠናቅው ሁሉም ተማሪዎች ወደ ተቋሙ ሲመለሱ ግን የተማሪ ህብረት ካፍቴሪያ ጉዳይ ተወካዮች የምግብ ግዕባት አቅርቦት ጥራት ቁጥጥርና ክትትል ስራቸውን አጠናክረው ይቀጥላሉ።

- የተማሪዎች ምግብ ቤት የተዘጋጀ የአገልግሎት እስታንዳርድ እንዳለው ይታወቃል ስለሆነም ምግብ ቤቱ የአንድ ተማሪ የዕለት ምግብ ፍጆታ እስታንዳርድን መሰረት ባደረገ መልኩ በ ቀን ተማሪ 1 እንጀራ ፍጆታ የተሰላ ሲሆን በዕየለቱ ባለው ተማሪ ቁጥር ልክ እንጀራው ተቆጥሮ ወደ ተማሪዎች ካፍቴሪያ ገቢ የሚደረግ ሲሆን አልፎ አልፎ በቂ ዳቦ በማይቀርብበት ሰዓት እና ዘግይቶ ወደ ተቋሙ በሚመጣበት ወቅት በዳቦ ምትክ ተማሪዎች እንጀራ እንዲመገቡ ይደረጋል።

- ከዚህ ቀደም በግቢው ውስጥ የሚገኘው የዳቦ መጋገሪያ አገልግሎት መሰጠት ጀምሮ እንደነበር ይታወቃል። ነገር ግን በነበረው ከፍተኛ የሆነ የሃይል አቅርቦት ውስንነት፣ በግቢው ውስጥ የሚገኘው ጀነሬተር የዳቦ ማሽኑን ማንቀሳቀስ አለመቻል፣ እና የማሽኑ የማምረት አቅም ተቋሙ ካለው የተማሪ ቁጥር ጋር ያልተመጣጠነ መሆኑ ጋር ተያይዞ ለተማሪዎች በቂ ዳቦ ማቅረብ ባለመቻሉ ምክንያት በዘላቂነት የዳቦ ማሽኑንን አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አልተቻለም። ሆኖም የተቋሙ የሃይል አቅርቦት ከተስተካከለ እና ተጨማሪ የዳቦ ማሽን ከተገዛ በሙሉ አቅም ወደ ምርት በመግባት በቂ የተማሪ የዳቦ አቅርቦት ማረጋገጥ ይቻላል።

8 <u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>

8.1 <u>በሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ በግኘ ሂደት የታዩ ድክመቶችን በተመለከተ፤</u>

8.1.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል ሁለት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች አይነት ቁጥር 6 አጠቃላይ ደረጃዎች ንዑስ አንቀጽ ቁጥር 5 የሥራ አመራሩ በስጋት ተጋላጭነት ትግበራና ትንተና እርምጃ መውሰድ እንዲችል በመ/ቤቱ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ላይ ያስጋት ተጋላጭነት

ፍተሻ በየጊዜው መደረግ እንዳለበት ይደነገጋል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እንደተመለከትነው ተቋሙ በፖሊሲ ደረጃ የስጋት ተጋላጭነት /Risk policy management/ እንዳላስቀመጠ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ የቻልን ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ትኩረት አድርጎ ተቋሙ እንደ ተቋም ጠንካራ መሰረት ሊኖረው ስለሚገባ በዋናነት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባ ዝርዝር ሁኔታዎችን እንደሚከተለው ተገልጸዋል ፡-

- የንብረት አስተዳደር ስርዓት /Asset management/: ዩኒቨርሲቲው በእጁ የሚገኙትን የመንግስት ንብረት ለአደጋ እና ለምዝበራ ወይም ለብክነት እንዳይጋለጡ መንግስት ያስቀመጠው መመሪያ እንዳለ ሆኖ ዩኒቨርሲቲው ይበልጥ የቁጥጥር ስርዓቱን ለማጠናከርና የአጠባበቅ ስርዓቱን ይረዳኛል የሚለውን የአሰራር ስርዓት በፖሊሲ ደረጃ ያላስቀመጠ መሆኑ፡፡
- የወጪ አስተዳደር ስርዓት /Expenditure management/ ዩኒቨርሲቲው የወጪ ሂሳብ አጠቃቀም ስርዓቱ መንግስት ያስቀመጠው መመሪያ እና ደንብ እንዳለ ሆኖ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን ለማጠናከር ፕላንና ፕሮግራምን መሰረት ያደረገና ወጪዎቹ ለታለመለት አላማ መዋላቸውን ሊያረጋግጥ የሚችል ወጪ ቆጣቢ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ከብክነትና ከስጋት መጠበቅ የሚያስችለውን የመፍትሄ ሃሳብ በፖሊሲ ደረጃ ያላስቀመጠ መሆኑ፡፡
- የግዥ አስተዳዳር ስርዓት /purchase management / የዩኒቨርሲቲው የግዥ ስርዓትን በተመለከተ የመንግስት ደንብ እና መመሪያ እንዳለ ሆኖ ይበልጥ የቁጥጥር ስርዓቱ ሊጠናከር የሚችል አመታዊ የግዥ ፍላጎትና ዕቅድን ማዕከል ያደረገ የግዥ ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ ከግዥ ጋራ ተያይዞ ለሚነሱ ጉዳዮች መልስ ይሰጥ ዘንድ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን ሊረዳ የሚችል የስጋት ተጋላጭነትን በመለየት የመፍትሄ ሃሳብ ሊሆን የሚችል በፖሊሲ ደረጃ ቀርጾ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሰው ሀብት አስተዳደር ስርዓት /personal management/ ዩኒቨርሲቲው የሰው ሀብት አጠቃቀም ስርዓቱ በተመለከተ በተቋሙ የሠራተኞች ፍልሰት በተለያየ ምክንያት ሊገጥም ስለሚችልና በተቋሙ ስራዎች አንዱ የስጋት ምንጭ ስለሚሆን ዩኒቨርሲቲው የመንግስት መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ሠራተኞቹን ለማቆየት

እንዲያስችለው የተለያዩ አጋጣሚዎችን መፍጠር የሚያስችል የአሰራር ስርአቶችን በመዘርጋት በፖሊስ ደረጃ ያላስቀመጠ መሆኑ፡፡

- ምዝበራ /Fraud / ዩኒቨርሲቲው ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ለምዝበራ ተጋላጭ የሆኑት ወይም ከፍተኛ የገንዘብ ፍሰት የሚታይባቸውን አካባቢዎች የመንግስት መመሪያ እና ደንብ እንዳለ ሆኖ ይበልጥ የቁጥጥር ስርዓቱን ሊያጠናክር የሚችሉትንና ከምዝበራ ለመከላከል የሚያስችለውን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና ከተቀመጠው ደንብና መመሪያ ውጪ ተፈፅሞ ቢገኝ ሊወሰድ የሚችለውን እርምጃ ሰራተኞች ሊያውቁትና ሊረዱት በሚያስችል መልኩ የአሰራር ስርዓቱን በፖሊሲ ደረጃ ያላስቀመጠ መሆኑ፡፡
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ዩኒቨርሲቲው ከሚሰጣቸው አገልግሎት ከመማር ማስተማር እና ከሙያ ስነ-ምግባር አንፃር ሊከሰት የሚችለውን የስጋት ምንጭ በመለየት የመፍትሄ ሃሳቦችን ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የትምህርት አሰጣጥ እና ጥራት ጋር ተያይዞ ሊመጡ የሚችለውን የስጋት ምንጮችን በመለየት የመከታተያ መርሃ ግብር በፖሊሲ ደረጃ ያላስቀመጠ መሆኑ ፡፡
- የመረጃ ግንኙነት ስርዓት /information communication technology/ ዩኒቨርሲቲው የICT ፖሊሲ አጠቃቀም ስርዓት በማስቀመጥ የዩኒቨርሲቲው የሆኑ መረጃዎች ለሶስተኛ ወገን ተላልፈዉ እንዳይሰጡ እና ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ፈሶባቸው የሚገዙ ሶፍት ዌሮች (soft wares') በሌሎች ግለሰቦች እጅ እንዳይገቡ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት የስጋት ምንጮችን ሊቀንስ የሚችልበትን የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፡፡ በተጨማሪም የተቋሙ መረጃዎች ከአደጋ ለመጠበቅ የሚያስችለውን /Disaster Recovery plan/ በፖሊሲ ደረጃ ያላስቀመጠ መሆኑ፡፡
- የትራንስፖርት ስምሪት አገልግሎትና አስተዳደር/ Transport service and vehicle management /ዩኒቨርሲቲው በትራንስፖርት አግልግሎት አሰጣጥ እና አጠቃቀም ዙሪያ የመንግስት መመሪያ እና ደንብ እንዳለ ሆኖ የቁጥጥር ሰርዓቱን ያጠናክርልኛል ብሎ የሚያስበውን የስጋት ተጋልጭነት በመለየት የመፍትሄ ሃሳቦችን በፖሊሲ ደረጃ ቀርጾ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። ለአብነት ያህል፤-የነዳጅ አጠቃቀምን፤ የጥገና አገልግሎትን ፤የንብረቶችን አጠቃቀም፣ የሃላፊዎች፣የሰራተኞች ፤የፑል ስራ የሚሰሩትን በመለየት የነዳጅ ፍላጎታቸውን ፤

የተሸከርከሪ አጠቃቀምና ለአደጋ ጊዜ አስፈላጊ የሆኑትን መሣሪያዎችን የመያዝና የአጠቃቀም ስርዓትን የማሳወቅ ስራ በመስራት ተግባራዊ ቢደረግ የተሻለ ነው ብለን እናምናለን፡፡

- የስነ-ምግባር ስርዓት /Code of Ethics /ዩኒቨርሲቲው በተለይ ከስነ ምግባር ጋር ተያይዞ በግዥ ፤በአገልገሎት አሰጣጥ፤በመልካም አስተዳደር ፤በመማር ማስተማር ፤ከሙያዊ ስነ ምግባር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ፤ ከመረጃ አያያዝና አጠባበቅ፤ በወጪ አጠቃቀም እና አፈ.ቃቀድ ,ዙሪያ የሚነሱ ጉዳዮች የተቋሙን ስም ሊያበላሹ ስለሚችል ዩኒቨርሲቲው የስጋት ተጋለጭነት ፓሊሲ በማዘጋጀት ለተቋሙ ሰራተኞች የማሳወቅ እና በእጃቸው እንዲደርስ ማድረግ እንዳለበት ሆኖ ፓሊሲው በተቋም ደረጃ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
- ዩኒቨርሲቲው ጨረታ በጋዜጣ በሚወጣበት ወቅት አብዛኛው መህበረሰብ ዘንድ የሚደርስውና መነበብ የሚችለው አዲስ ዘመን ጋዜጣ መሆን ሲገባው ሄራልድ የሚጠቀሙ በመሆኑ በቂ የግዥ ተጫራች የማይቀርብ መሆኑን
- የሠራተኞች የስራ ሰዓት መግቢያና መውጫ በትክክል ቁጥጥር የማይደረግበት በመሆኑ፤
- የህግ አሰተዳደር/Law Management /ዩኒቨርሰቲው በውስጥም ሆነ በውጪ የሚገጥሙት ችግሮች ከዩኒቨርሲቲው መስፋት ጋር አብሮ የሚያድጉ ስለሆነ የችግር አፋታት ስርዓቱን ፣ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት ቅድመ ጥንቃቄዎች ፣ችግሮች ከተከስቱ በኃላ ያዋጣል አያዋጣም የሚለውን ሊያሳይ የሚችል የአሰራር ስርዓት በፓሊሲ ደረጃ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ስለዚህ የዩኒቨርሲቲው የህግ ክፍል በሰው ሃይል አደረጃጀት በማስተካከል መንግስት ማግኘት ያለበትን ጥቅም ማጣት ስለማይገባው ይህን ችግር ሊፈታ የሚችል የስጋት ተጋላጭነቱን ሊቀንስ የሚያስችል አሰራር በፖሊሲ ደረጃ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

8.1.2 ***ሥጋት፤***

የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት ተደርጎ የመፍትሄ አቅጣጫ ካልተቀመጠ በሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ዩኒቨርሲቲው ዓላማውን እንዳያሳካ እንቀፋት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

8.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ በየጊዜው ቢደርግ በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ደካማነት የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግርችን ለይቶ ቅድመ ጥንቃቄ ለመውሰድ የሚኖረውን ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በመመሪያው መሰረት የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይኸውም በንብረት አመዘጋገብና አጠባበቅ፣ በገቢ አሰባሰብ፣ በወጪ አስተዳደር፣ በግዥ አፈጻጸም፣ በሰው ሀብት አስተዳደር፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በመረጃ ግንኙነት ስርዓት፣ በተሽከርካሪዎች አጠቃቀምና አጠባበቅ ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት ይገባል፡፡

8.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

የፌዴራል መንግሰት የውስጥ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 8 ተከትሎ በመ/ቤታችን ደረጃ የስጋት ቦታዎችን በመለየት የተጋላጭነት ደረጃቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ችግሮች እንዳይከሰቱ ቀደሞ ዩኒቨርሲቲውን ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ተግዳሮቶች የሚከላከልበትና የተከሰቱትንም ችግሮች ወቅታዊ ማላሽ የሚሠጥበት አሰራር ያለ ሲሆን ይህም በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የሚመራ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ካውንሰል የተቋቋመና እቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን አላማውም ዩኒቨርሲቲው ተልዕኮውን እንዳያሳካ እንቅፋት ሊሆን የሚችሉ ስጋቶችን በሁሉም የስራ ክፍሎች በመለየትና ተከታትሎ መፍትሄ የሚሠጥበትን አሰራር እንዲሠጥ ነው፡፡ ካውንስሉ ሁሉንም የስራ ክፍሎች ያካተተ የስጋት ዳሰሳ ሥራ በቀጣይ እንዲሠራ የሚደረግ መሆኑን እንገልፃለን ፡፡

9. የጨረታ ሂደትና ውል አስተዳደርን በተመለከተ

9.1 ግኝት፣

አዋጅ ቁጥር 649/2001 የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ምዕራፍ ሦስት አንቀጽ 28 የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት በሚመለከት በማንኛውም የመንግስት ግዥ ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከግዥው ልዩ ባህሪይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

- በዋናው ግቢ ግልጽ ጨረታ በሚወጣበት ወቅት ዩኒቨርሲቲው በቂ ተጫራች ለማግኘትና የሚፈልገው ዕቃ ግዥ ለመፈጸም ሁሉም ተጫራቾች እድሉ እንዲያገኙና በብዛት በሀገሪቱ ተነባቢ የሆነ ጋዜጣ ለጨረታ መጠቀም ሲገባ በተደጋጋሚ ሄራልድ ጋዜጣ ላይ በማውጣት አብዛኛው ጊዜ በቂና አቅም የ ያላቸው ተጫራቾች የማይቀርቡ መሆኑ፣

- ግዥ ሰራተኞች ቀድመው ለሚወስዱት የቅድመ ክፍያ ሂሳብ ድጋሚ ከመውሰዳቸው በፊት ተገቢው ማስረጃ አቅረበው በወቅቱ አቅረበው የማይወራረድ መሆኑ፤

9.1.2 ሥጋት

- በሚፈለጉ ዕቃዎች ካልቀረቡ የሚፈለግባቸው ጥቅም ላይሰጡ ለተፈለገው አገልግሎት ለይውሉ ይችላል፡፡
- በጨረታ የሚፈጸሙ ግዥዎች ላይ ተወዳዳሪዎች ማቅረብ የሚገባቸው ሰነዶች ሳያቀርቡ በውድድር ውስጥ የሚሳተፉ ከሆኑ ህጋዊነትን ላያበረታታ ይችላል፡፡
- ብቁ ያልሆኑ ተወዳዳሪዎችም በጨረታው ሊሳተፉና ሊያሸንፉ ይችላሉ፡፡

9.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ፤

ግዥዎች በጨረታ መፈጸም ጊዜ በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያው መሠረት ሊፈጸሙ ይገባል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ የጨረታ በሚታወጅበት ወቅት በሀገሪቱ በብዛት ተነባቢ በሆኑ ጋዜጦች ጨረታ መውጣት አለበት፡፡

9.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

ዩኒቨርሲቲው በስሩ የሚገኙትን የስራ ሂደቶች ሊኖራቸው የሚችለውን የስጋት ተጋላጭነት እና የቦታዎች ተስማሚነትን በመለየት የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ገሚሶቹ ወደ ስራ የተሸጋገሩ ሲሆን ቀሪዎቹም በዚሁ አግባባ በቅርቡ ተፈጻሚ የሚሆኑ ይሆናል፡፡

10. ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት እርምጃ የተወሰደባቸውን እና ያልተወሰደባቸውን የሚያሳይ ዝርዝር፤

ግኝት፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምሰት አንቀጽ 17/3 መሰረት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን እርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው እና የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው በተገለፀው መሰረት ለዩኒቨርሲተው በ 2012 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ለማጣራት ኦዲት ሲከናወን፤

ተ.ቁ	የ 2012 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች	በግኝቱ ላይ የተሰጠ የማሻሻያ ሀሳብ	እርምጃ		የተወሰደው እርምጃ
			ከተወሰደ	ካልተወሰደ	
			√	x	
1.	ዋናው ግቢ ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ በሳጥን የሚያዝ ጥሬ ገንዘብ በደንብና መመርያው መሰረት ብር 100,000.00 መሆን ሲገባው ሰኔ 30/2012 በውስጥ ኦዲት በሳጥን ተገኝቶ የተቆጠረው እና ለገንዘብ ሚኒስትር በፈሰስ ሪፖርት የተደረገው ጥሬ ገንዘብና ሰነድ ብር 302,746.91 መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡	የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡		X	እንደሚታወቀው ማንኛውም ክፍያ መፈፀም ያለበት በባንክ አማካኝነት በተከፋይ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በኩል መሆኑ ይታወቃል፤ ይሁን እንጅ በወቅቱ አዲስ የተቀጠሩ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች የባንክ መረጃ በወቅቱ ካለማቅረባቸው ባሻገር እንዲሁም ለተለያዩ መምህራን አስቸኳይነት ለነበራቸው የመስክ ጉዞ ወጪ መሸፈኛ የሚውል በገንዘብ ያዥ አማካኝነት ከባንክ ወደ ሳጥን ተላልፎ ተከፋይ በመከፈሉ ምክንያት የሣጥን የጥሬ ገንዘብ መጠን በብልጫ ሊስተዋል ችሏል፡፡ ይሁን እንጅ ለሰራተኞች መሰል ክፍያዎች በጥሬ ገንዘብ መፈፀም እንደማይገባ እና በዚሁ አግባብ የመመሪያ ድጋፍም እንደሌለው በማስገንዘብ አብዛኛዎቹ ክፍያዎች በባንክ በኩል እንዲከናወኑ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን በቀጣይ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሰረት ተከትለን አቅም በፈቀደ ሁሉ ተግባራዊ የምናደርግ ይሆናል፡፡

2.	በመመሪያው መሰረት ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ላይ የታክሱን ሂሳብ ተቀናናሽ የሚያደርገው የአንድ ጊዜ ግብይት ዋጋ 5,000.00/አምስት ሺህ/ በላይ ሲሆን ግብርን ቀንሶ ማስቀረት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በጠቅላላ ድምር ብር 614,863.04 ከድርጅቶቹ ተቀናሽ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲገባዉ አላግባብ ከነተ.እ.ታክሱ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን ለኦዲት በቀረቡ የናሙና ሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡	ከላይ ከመመሪያ ዉጪ ከድርጅቱ ተቀናሽ ሳይደረግ ክፍያ የተፈጸመዉ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገንዘብ ተመላሽ ተደርጎ ለሚመለከተዉ አካል ፈሰስ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊትም ዩኒቨርስቲዉ በመመሪያና ደምብ መሰረት ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል፡፡		X	ከድርጅቶቹ ተቀናሽ በማድረግ ተመላሽ መሆን ካለበት ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ብር 614,863.04 ውስጥ 86.46% (531,666.24) እንዲመለስ በማድረግ ማስተካከያ የወሰድን ሲሆን በቀጣይ ከትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቱ ቀሪ/ በብልጫ/ የተከፈለውን የተ.እ.ታ ሂሳብ ብር 83,196.80 ሰብስበን ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲሆን በማድረግ ሙሉ በሙሉ ለቀረበው ግኝት የማስተካከያ እርምጃ የምንወስድ ይሆናል፡፡
3.	ዩኒቨርስቲዉ {presenter and, discussant in senior and fresh student meeting] ስብሰባ ለተሳተፉ በሚል ለ257 የአካዳሚክ ሰራተኞች አላግባብ በመማር ማስተማር የትርፍ ሰዓት/በክሬዲት ሀወር/ የተጣራ ብር 240,325.30፣ ለአዲስ እና ነባር ተማሪዎች በማህበረሰብ ስልጠና ወቅት ዋና ኮሚቴ ሆነዉ ለተሳተፉ እና ድጋፍ ላደረጉ ለ83 የአስተዳደር ሰራተኞች አላግባብ በመማር ማስተማር የትርፍ ሰዓት/ክሬዲት ሀዉር/ የተጣራ ብር 250,368.35፣ በጠቅላላ ድምር ብር 490,693.65 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡	አላግባብ ወጪ የተደረገዉ ገንዘብ ተሰብስቦ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም የዩኒቨርሲቲዉ ኃላፊዎች በመንግስት በተላለፈው ሰርኩላር መሰረት ስልጠናዎችና ስብሰባዎች በአነስተኛ ወጪ ሊከናወን ይገባል፡፡		X	በተጠቀሰው የነባር እና የአዲስ ገቢ ተማሪዎች በማህበረሰብ አገልግሎት ስብሰባ እና ስልጠና በተካሄዱበት ወቅት የአካዳሚክና የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛው የመማር ማስተማር ተግባር ባሻገር በቀጥታ በተካሄዱት ስልጠናዎች ላይ መምህራት ተማሪዎችን ያሰለጠኑ ሲሆን፣በአንጻሩ የአስተዳደር ዘርፍ የስራ ኃላፊዎች በነበሩት ስብሰባዎች እና የስልጠና መርዓ ግብሮች ላይ ለነበራቸው የሃላፊነት እና የስራ ድርሻ አበርክቶት ተከፋይ የሆነ ሲሆን፣ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ስልጠናዎቹና ስብሰባዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ በተሳካ ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆን የተጣለባቸውን የስራ ሃላፊነት በአግባቡ በመወጣታቸው ሳቢያ የዩኒቨርስቲው የስራ ኃላፊዎች የሀገሪ በመገንዘብ በሰጡት የክፍያ የስራ ቃለዛዘ መሰረት

					ለስብሰባና ለስልጠና ተሳታፊዎች ክፍያው ሊፈጸም ችሏል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ የቀረበውን የኦዲት ግኝት ዋቢ በማድረግ በተቀመጠው የፋይናንስ ህጉ መሰረት ስልጠናዎችና ስብሰባዎችን በአነስተኛ ወጪ እንዲካሄዱ በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ላይ እንገኛለን፡፡
4.	**በዋናው ግቢ** ከተወከል ጠቅላላ ትራንስፖርት ድርጅት ጋር የተለያዩ የትምህርት ክፍል ተማሪዎችን ከጅግጅጋ ወደ ሀረር ሲሄዱ በቀን ብር 4,300.00 በወር 129,000 ከጅግጅጋ ወደ ድሬዳዋ ሲሄዱ በቀን ብር 5,160.00 በወር 154,000 እና የሪፈራል ሆስፒታል ደግሞ ከሆስፒታሉ ወደ ጅግጅጋ ከተማ ለማመላለስ በቀን ብር 2,667.00 በወር 80,000.00 ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ የላይበራሪ ሰራተኞችን ከዩኒቨርስቲው ወደ ጅግጅጋ ከተማ ለማመላለስ ውል ሳይገባ አገልግሎት መገኘቱን ይህም ሆኖ ሆስፒታሉ የገባውን ውል ርቀታቸው ተመሳሳይ ስለሆነ ከሆስፒታሉ ወደ ከተማ ከመጠቀም ይልቅ ከጅግጅጋ ወደ ሀረር እና ከጅግጅጋ ወደ ድሬዳዋ ለማመላለስ በተገባ ውል ተመን ክፍያ በመፈጸሙ አለአግባብ በብልጫ ብር 394,600.00 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፡፡ **በሀሰን የበሬ ሪፈራል ሆስፒታል** ከታረቀኝ ነጋሽ የደረቅ ጭነት አገልግሎት ድርጅት ጋር የግቢ ሰራተኞቹን ለማመላለስ ከህዳር 12/2012 ጀምሮ በየወሩ ሰማንያ ሺህ/80,000/ ለመክፈል ዉል የገባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በቀን 23/3/2012 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 576803 ሆስፒታሉ ዉል ከተያዘበት ከህዳር 12 ቀን ጀምሮ ብር **50,666.37=** (80,000/30*19} ለድርጅቱ መክፈል ሲገባዉ አላግባብ ሙሉ የህዳርን ወር ብር 80,000 በመክፈል ብር **29,333.37**=(80,000/30*11} በብልጫ	ከላይ የተጠቀሰዉ ገንዘብ ከሚመለከተዉ አካል ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የዚህ አይነት ብልሹ አሰራር እንዳይከሰት አስፈላጊውን ጥንቃቄ የበላይ አመራሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡		X	ከሚመለከታቸው የስራ ሓላፊዎች እና ከአገልድሎት ሰጪ ድርጅቱ ጋር በጉዳዩ ዙሪያ በመወያየት ለቀረበው ግኝት የዕርምት እርምጃ የምንወስድ ይሆናል፤ **ሃሰን የበሬ ሪፈራል ሆስፒታልን በተመለከተ**፡ለትራንስፖረት በብልጫ የተከፈሌ ኪፍያን በተመለከቱ፣ ከኦድት ግኝት በተለኬልን መሰራት የ 2012 በጀት አማት ኦድት ስዳራግ ሆስፒታሉ ግልፅ ጨራታ በመዉጣት ከተራቁኝ ነጋሽ የደራቅ ጭናት አካራይ ገር የሆስፒታሉን የኦክስጅን ስልንዳር ከጅግጅጋ ወደ አድስ አበባ ለመመለለስ ዉል በመግበት በወሩ 80,000ሺ ብር የሚንከፍል መሆኑን ኢንገልፃሌን፡፡ ሆኖም ግን ሆስፒታሉ የወራ ህዳር ኪፍያን ስከፍል የ19 ቀን ክፍያ መክፋል ስገበዉ ሙሉ የወሩን ክፍያ መክፋሉን እያገለፅን ይህ ልሆን የቻለዉ ዉሉ በየወሩ የአገልግሎቱን ኪፍያ መክፋል አሌበት ስለሚል በቀን ስሌት ተሰርቶ መክፋል ስላማንችል ሀሳቡም እንዳይዘበቢን በገዚህ ሚክንት ሙሉ ኪፍያ ለመክፈል ችሌናል ሆኖም ግን በዉሉ መጠነቀቅያ መላትም ወራ ህዳር 2013 ምንም አይነት ክፍያ

	የተከፈለ መሆኑን፣ በጠቅላላ ድምር ብር 423,933.37 በዋናው ግቢ እና በሆስፒታል ለትራንስፖርት በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡				የማይከፈል መሆኑ በዝዉ እናሳዉቃለን፡፡ ከኦዲት በተላከልን ሪፖርት መሰረት ከዚህ ቀደም የውሃ ማመላለሻ ቦቴ የግንቦትና ሰኔ ወር ቅድሚያ ክፍያ የከፈልንበት ምክንያት የመኪናው ባለቤት በወቅቱ መኪናው ጥገና የሚያደርግበት አቅም የለኝም ብሎ ሪፖርት በማድረጉ የሆስፒታሉ የውሃ አገልግሎት ከሚቋረጥ የሁለት ወር ቅድሚያ በመክፈል አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ አድርገን ነበር፡፡ አሁን ግን ምንም አይነት ቅድሚያ ክፍያ የማንፈጽም መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ ዋናው ግቢ፡- የመነሻ የውል ስምምነት ሰነዱና የክፍያ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ የማስተካከያ እረምጃ የምንወስድ ይሆናል፡፡
5.	በድምሩ ብር 314,670,825.82 ውል የተገባ ስድስት ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከተ.ቁ.1-4 የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሳይያዝ ብር 88,600,619.52፣ ከተ.ቁ.1-6 ለውላቸው የውል ማስከበሪያ ሳይያዝ ብር 31,467,082.58 ውል መገባቱን በድምሩ ብር 120,067,702.10 ተመጣጣኝ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እና የውል ማስከበሪያ ሳይያዝ ፕሮጀክቶች በተቋራጭ ስራ የተጀመሩ ቢሆንም በተቋራጮች መጥፋት እና ተቋራጮች አፈጻጸም ድክመት ምክንያት በአሁኑ ወቅት ፕሮጀክቶቹ መቋረጣቸውን ከነዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 21,225,396.49 በስራ ተመላሽ መደረጉን እና ቀሪው በድምሩ ብር 98,842,305.61 ከጉዳት ካሳ ውጭ ከተቋራጩ የሚፈለግ መሆኑን ለማረጋገጥ	ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት በቅድሚያ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በውሉ ውስጥ ሊከፈል እንደሚገባ የሚገልጽ አንቀጽ የተካተተ ስለመሆኑ ማረጋገጥና ለሚፈጸመው ክፍያም በቅድሚያ ተመጣጣኝ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና መያዝ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም		X	ውላቸው ከተቋረጠ የግንባታ ስራ ተቋራጭ ለባንክ ብሩ ተመላሽ እንዲሆን የተጻፈና ብሩን ተመላሽ ለማድረግ የክፍያ ማቋረጫ (Payment Termination) በአማካሪው አለመቅረቡና ይህን ሒደት በቅርበት መከታተል የነበረበት የምህንድስ እና ግንባታ ዳይሬክቶሬት ኃላፊነታቸውን በወቅቱ ባለመወጣታቸው ገንዘቡ ሊሰበሰብ አለመቻሉ ይታወቃል። ሆኖም ግን አሁን ለባንኩ በድጋሚ ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርጉልን ደብዳቤ የተጻፈ የቅርብ ክትትል

	ተችሏል፡፡	ተመጣጣኝ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ያልተያዘላቸውን አቅራቢዎች እንዲያቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡ ተቀጽላ ሊጀር ያልተከፈተላቸውም ሊከፈትላቸው ይገባል፡፡ ለውሉ የውል ማስከበሪያ መያዝ ይገባል፡፡ በቀጣይም የሚመለከተው አካልም ተመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ጥንቃቄ በማድረግ ይህንን ስህተት በሰሩ ባለሙያዎች ላይ የማስተካከያ ርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡			በማድረግ ላይ እንደምንገኝ በገልጽነው መሰረት የክፍያ ማቋረጫ(Payment Termination) ተቀናንሶ ተቋራጩ በሀግ የሚመለስ ብር የውል ማስከበሪያውን ሰይጨምር ነው በክፍያ ማቋረጫ (Payment Termination) በቀረበው መሰረት የትርጉም ስራ ተሰርቶ ክስ ለማቅረብ እየተሰራ እንደሆነ እንገልጻለን።
6.	በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ በተሰጠን የአቅራቢዎች የተሰብሳቢ ሂሳብ መግለጫ መሰረት ከ5 ድርጅቶች በድምሩ ብር 8,125,862.61 በተገባው ውል ውስጥ ቅድሚያ ክፍያ ሊፈጸም እንደሚችል ባልተካተተበት ሁኔታ እንዲሁም ለቅድሚያ ክፍያው ተመጣጣኝ ዋስትና ሳይያዝ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ተቀጽላ	ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት በቅድሚያ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በውሉ ውስጥ ሊከፈል እንደሚገባ የሚገልጽ አንቀጽ የተካተተ ስለመሆኑ ማረጋገጥና ለሚፈጸመው ክፍያም በቅድሚያ ተመጣጣኝ		X	ከአማሬሳ የዘይት ፋብሪካ ለተማሪዎች የምግብ ዘይት ግዥ ለሚፈጸም ክፍያ ወዲያውኑ ግብአትን ከተፈላጊ ማስረጃ ጋር የሚሰጥ በመሆኑ እና ለጅጅጋ ፖሊ ቴክኒክ የተፈጸመው የአገልግሎት ክፍያ በተመሳሳይ የመንግስት ተቋም በመሆኑ

	ሌጀርም ያልተከፈተላቸው ሂሳቦች መኖራቸውን በተሰጠን መግለጫና በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡	የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና መያዝ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ተመጣጣኝ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ያልተያዘላቸውን አቅራቢዎች እንዲያቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡ ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተላቸውም ሊከፈትላቸው ይገባል፡፡ በቀጣይም የሚመለከተው አካልም ተመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡			ሊሰጥ የሚችለው መያዣ ያለመኖሩን እየገለጽን፣ የሌሎችን አቅራቢች በተመለከተ የቅድመ ክፍያ ዋስትና የሰነድ አያያዝ የአሰራር ክፍተት በግኝ ክፍሉ የነበረ ሲሆን ለዚህም በተዋረድ የዕርምት እርምጃ ተወስዷል፡፡ በቀጣይ መሰል የአሰራር ክፍተት እንዳይስተዋል ትኩረት ሰጥተን የምንሰራ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
7.	ዩኒቨርስቲ በግንባታ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች እንዳሉ በተቋሙ መረጃ የቀረበ ቢሆንም ለተቋራጮቹ በእያንዳንዱ ፕሮጀክቶች ስም ተሰብሳቢና ተካፋይ ተቀጽላ ሌጀሮች እንዳልተከፈተ በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡	ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለእያንዳንዱ ለተጀመሩ ፕሮጀክቶች በየፕሮጀክቶች ስም ተቀጽላ ሌጀር ሊከፍት ይገባል፡፡		X	ከላይ በግኝቱ የተገለፀው በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ስም ተሰብሳቢና ተከፋይ ተቀፅላ ሌጀር ያልተከፈላቸው ተብሎ የቀረበው ስህተት ሲሆን በኦዲት ወቅት የእያንዳንዱ ፕሮጀክት ለተቆራጮች የተከፈለውን ቅድመ ክፍያ ዝርዝር እና ቀሪ ተሰብሳቢ ሂሳብ በእያንዳንዱ ተቋራጭ ምን ያክል እንደሚፈለግ የሚገልጽ ሪፖርት እንዲቀርብ በተጠየቀው መሰረት የእያንዳንዱን ተቋራጭ የሚፈለግበትን ተሰብሳቢ ሂሳብ እስከ ተቀፅላ ሌጀራቸው የሚያሳይ ሪፖርት እንዳቀረብን ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ከላይ በግኝቱ የተገለጸው ተሰብሳቢ ተቀጽላ ሌጀር አልተከፈተላቸውም የሚለው ስህተት በመሆኑ እንዲስተካከል እን[illegible] [illegible]ን በተከፍሉ ሂሳብ መደብ 5061 የቀረበው የኦዲት ማስታወሻ [illegible] ሲሆን በእያንዳንዱ[illegible] ተቋራጭ

					የተቀነሰውን የretention ሂሳብ የሚታወቅ ቢሆንም ተቀፅላ ሌጀር መከፈት ስላለበት በቀጣይ ይህንን የምናስተካክል ይሆናል፡፡ በመሆኑም ከላይ በዝርዝር በቀረበው ማብራሪያ መሰረት ግንዛቤ እንደወሰድበት እንጠይቃለን፡፡

2.4.1 ***ሥጋት፣***

በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ በኦዲት ወቅት የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዳይታረሙ ከማድረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

2.1.1 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

አባሪ 1 ቤት ተሰጥቷቸው የቤት አበል የተከፈላቸው መምህራን

ተ.ቁ	የሰራተኛው ስም	የስራ ክፍል	የወር ክፍያ	ጠቅላላ ክፍያ
1	መ/ር እዮብ ውብሸት አበበ	ነርስ	800.00*12	9,600.00
2	መ/ት በርዋቆ ዱአሌ	ባይሎጅ	800.00*12	9,600.00
3	መ/ር ኢክራም ኢብራሂም	ኢንጅነሪንግ	800.00*12	9,600.00
4	መ/ር መኮንን መስቀሉ ሽገሬ	ነርስ	800.00*12	9,600.00
5	መ/ር ፈይሳ ሳዶ	ፊዚክስ	800.00*12	9,600.00
6	መ/ር ቢኒያም ዘውዴ ደሞዝ	ጆርናሊዝም	800.00*12	9,600.00
7	መ/ር ባሂር ሙሁመድ	ጤና መኮንን	800.00*12	9,600.00
8	መ/ር መሀመድ በዱ	ጅኦግራፊ	800.00*12	9,600.00
9	መ/ር ከድር መሀመድ	ግኦግራፊ	800.00*12	9,600.00
10	መ/ር አብዲፈታህ ኢልሚ	ጤና መኮንን	800.00*12	9,600.00
		ድምር		96,000.00

አባሪ 2 በሚያስተምሩበት ተቋም በትምህርት ላያ ላሉ መምህራን የተከፈለ የቤት አበል ክፍያ

ተ.ቁ	የመምህራን ስም	ብዛት	የቤት አበል	ጠቅላላ ገንዘብ
1	Farhan Abdi Yusuf	12 ወራት	700.00	8,400.00
2	Niama Ahmed Yusuf	12 ወራት	700.00	8,400.00
3	Muna Ahmed Hassen	12 ወራት	700.00	8,400.00

4	Ekarm Ibrahim Sehal	12 ወራት	700.00	8,400.00
5	Feriya Abdulahi Abtidoon	12 ወራት	700.00	8,400.00
6	Kalid Hassen Ibrahim	12 ወራት	700.00	8,400.00
7	Mohamed Abdi Ismael	12 ወራት	700.00	8,400.00
8	Mohamed Aden Gedi	12 ወራት	700.00	8,400.00
9	Mohammed Ali Ibrahim	12 ወራት	700.00	8,400.00
10	Abdirezak Mussa Omar	12 ወራት	700.00	8,400.00
11	Farhan Mahamed Tahir	12 ወራት	700.00	8,400.00
12	Fathia Budul Ismail	12 ወራት	700.00	8,400.00
13	Abdirahman Mohamud Shuriy	12 ወራት	700.00	8,400.00
14	Ismael Abdinasir Malin	12 ወራት	700.00	8,400.00
15	Sulub Yusuf Hassen	12 ወራት	700.00	8,400.00
16	Liban Abdilahi Abdi	12 ወራት	700.00	8,400.00
17	Mowlid Abdi Seid	12 ወራት	700.00	8,400.00
18	Abdallah Mahamed Malin	12 ወራት	700.00	8,400.00
19	Abebe Teklu G/hana	12 ወራት	700.00	8,400.00
20	Habib Muhumed Osman	12 ወራት	700.00	8,400.00
21	Abdifetah Hashi Abdi	12 ወራት	700.00	8,400.00
22	Mohamed Farah Ahmed	12 ወራት	700.00	8,400.00

23	Mohamed Iman Abdi	12 ወራት	700.00	8,400.00
24	Intsar Meder Ahmed	12 ወራት	700.00	8,400.00
25	Abdiwali Aden Guled	12 ወራት	700.00	8,400.00
26	Fatuma Ali Abdi	12 ወራት	700.00	8,400.00
27	Nimo Aden Mahamud	12 ወራት	700.00	8,400.00
28	Asma Ahmed Muse	12 ወራት	700.00	8,400.00
29	Abdurhaman Yusuf Abdulahi	12 ወራት	700.00	8,400.00
30	Abdikeni Mohamed Ahmed	12 ወራት	700.00	8,400.00
31	Nejib Ali Isma'el	12 ወራት	700.00	8,400.00
32	Abdishakur Aden Ahmed	12 ወራት	700.00	8,400.00
33	Kader Mohamed Ismael	12 ወራት	700.00	8,400.00
34	Tawakal bdi Ismael	12 ወራት	700.00	8,400.00
35	Fardowsa Osman Nur	12 ወራት	700.00	8,400.00
36	Najma Badir Mohamed	12 ወራት	700.00	8,400.00
37	Mohamed Abdalahi Aden	12 ወራት	700.00	8,400.00
38	Farhan Abdullahi Ibrahim	12 ወራት	700.00	8,400.00
39	Mohamed Abdikadir Mohamed	12 ወራት	700.00	8,400.00
40	Abdi Shafi Abdi	12 ወራት	700.00	8,400.00
41	Amina Mohamed Aden	12 ወራት	700.00	8,400.00

42	Neima Yusuf Mohamud	12 ወራት	700.00	8,400.00
43	Abdikadir Muhumed Mumin	12 ወራት	700.00	8,400.00
44	Kadra Ibrahim Abdi	12 ወራት	700.00	8,400.00
45	Mohamed Hassen Mahamed	12 ወራት	700.00	8,400.00
46	Ifrah Abdirizak Haro	12 ወራት	700.00	8,400.00
47	Muna Hajiibrahim Omer	12 ወራት	700.00	8,400.00
48	Omer Yusuf Mohamud	12 ወራት	700.00	8,400.00
49	Sayda Mohammed Mohammud	12 ወራት	700.00	8,400.00
50	Nardos Getachew Kebede	12 ወራት	700.00	8,400.00
51	Abdibaset Mohamed Aden	12 ወራት	700.00	8,400.00
52	Yosef Alemayehu Fikire	12 ወራት	700.00	8,400.00
53	Habon Bedi Ali	12 ወራት	700.00	8,400.00
54	Kedir Mohamed Ibrahim	12 ወራት	700.00	8,400.00
55	Ahmed Farah Abib	12 ወራት	700.00	8,400.00
56	Nimo Dawud Yasin	12 ወራት	700.00	8,400.00
57	Abdirahman Aw-muse muhamed	12 ወራት	700.00	8,400.00
	ድምር			**478,800.00**

አባሪ 3 ከአቅራቢዎች ላይ ያልተቀነሰ ጉዳት ካሳ

ቀን	የድርጅቱ ስም	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የውል የተጠናቀቀበት ቀን	ንበረት ገቢ የሆነበት ቀን	የገንዘብ መጠን	የዘገየ የቀን ብዛት	የቆረጥ የነበረበት ጉዳት ካሳ
20/12/12	Ahmed Ali	224725	19/01/13	07/03/13	3,030,250.00	48	145,452.00
12/04/13	Karamara foam	224724	26/12/12	24/03/13	5,261,250.00	88	486,299.00
26/05/13	Ayante Almunium	224726	12/01/13	24/03/13	1,587,000.00	72	114,264.00
25/02/13	Nasir Inportor	232066	03/08/12	20/01/13	1,211,456.00	167	121,145.60
ድምር							867,160.60

አባሪ 4 ግዥ ቀራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተፈጸመ

ተ.ቁ	ቀን	አቅራቢ ድርጅት	የሰነድ ዓይነት	የሰነድ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የብር መጠን
1	04/02/2013	Delta Printing Press	PV	232068	6215	185,640.00
2	04/02/2013	Delta Printing Press	PV	232069	6215	180,000.00
3	04/02/2013	Ethio printing	PV	232070	6215	190,000.00
4	04/02/2013	Ethio printing	PV	232098	6215	180,000.00
5	04/02/2013	Delta Printing Pres	PV	938346	6215	175,000.00
6	27/02/2013	Ethio Printing Press	PV	224161	6215	190,000.00
7	27/02/2013	Madbacada Dheman	PV	232057	6215	182,000.00

8	27/02/2013	Madbacada Dheman	PV	232056	6215	185,000.00
11	30/11/2012	Ayan Mahad	JV	727733	6213	194,856.00
12	13/01/2013	Bahar Nuredin	PV	232504	6212	194,999.99
13	28/01/2013	Shebelle Priniting	PV	232511	6213	195,247.00
14	04/02/2013	Shebelle Priniting	PV	232088	6213	194,263.73
15	29/02/2013	Shabelle Printing	PV	224152	6213	194,373.00
17	17/03/2013	Warda Mohamed	PV	224478	6213	196,770.75
18	17/03/2013	Ayan Mahad Awil	PV	224479	6213	194,930.75
19	30/03/2013	Nejashi Stashionary	PV	224536	6212	199,237.50
20	09/04/2013	Shabelle Printing	PV	224857	6213	198,966.33
21	22/04/2013	Shebelle Priniting	PV	224736	6213	199,410.00
22	22/04/2013	Shebelle Priniting	PV	224852	6213	194,672.60
23	22/04/2013	Nejashi Stashionary	PV	224853	6212	199,640.00
24	03/05/2013	Shebelle Printing	PV	232133	6213	198,501.50
25	03/05/2013	Shebelle Printing	PV	232140	6213	196,766.32
26	17/05/2013	Nejashi Stationry	PV	232215	6212	199,410.00
28	20/05/2013	Nejashi Stationry	PV	232216	6212	199,640.00
29	30/05/2013	Ayan Mehad Awil	JV	735737	6212	194,925.00
32	09/04/2013	Shebelle Priniting	PV	224858	6213	192,395.00

ድምር	5,006,645.47

<u>አባሪ 5 ከውሉ ውጭ ገቢ የተደረገ መጽሐፍ ግኝ</u>

ተ.ቁ	የመጸፍቶች ዓይነት	ብዛት	የአንዱ ዋጋ	ገንዘብ
1	አጭር ና ቀላቀል የአማረኛ ሰዋስው	10	400.00	4,000.00
2	essential of cell biology	1	3,100.00	3,100.00
3	junquerias basic histology text and atlas	2	400.00	400.00
4	Microbiology	1	3,600.00	3,600.00
5	Biochemistry	2	3,200.00	6,400.00
6	Biochemistry	2	2,900.00	5,800.00
7	essential of economics	20	400.00	8,000.00
8	economic development	2	600.00	1,200.00
9	ten steps to advancing college reading skills	1	3,000.00	3,000.00
10	international law	2	2,700.00	5,400.00
11	Ethiopian constitution development book Vol I	2	3,220.00	6,440.00
12	Mathematics an introduction	1	900.00	900.00
13	Pathologic basic of disease	2	3,400.00	6,800.00
14	Practical guide to project planning	2	3,100.00	6,200.00
15	public adminstration an introduction	2	2,100.00	4,200.00
16	fundamental of physics	7	3,300.00	23,100.00
17	introduction to global politics	2	1,050.00	4,200.00
18	Comparative politics of third world linking concept& cases	1	1,900.00	1,900.00
19	international relation	3	3,050.00	9,150.00
20	cases comparative politics	2	2,850.00	5,700.00
21	international law &politics	1	3,000.00	3,000.00
22	Essentials of reading world politics	1	3,100.00	3,100.00
23	Essentials of understanding psychology	2	2,800.00	5,600.00
24	cultural anthropology	4	2,350.00	9,400.00
25	development &adapted physical education	5	2,260.00	11,300.00
26	Veterinery parasitology at aglance	2	4,700.00	9,400.00
27	Atexbool of veterinery special pathology	2	3,800.00	7,600.00
	ድምር			**158,890.00**

አባሪ 6 የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ

ከ10% በላይ ያልተሰራበት ከጀት በላይ ወጣ የሚያሳይ ሂሳብ ዝርዝር፤

መደበኛ በጀት

የወጪ ሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ስራ ላይ የዋለ በጀት	የሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው የወጪ ሲሳብ በጀት		
			ስራ ላይ ያልዋለ	በላይ ወጣ	
6113	12,328,000.00	18,187,123.02		5,859,123.02	48%
6115	49,608,000.00	52,096,781.86		2,488,781.86	5%
6121	45,450,000.00	36,428,626.20	9,021,373.80		20%
6124	5,620,000.00	5,804,452.11		184,452.11	3%
6131	41,065,395.00	34,682,452.11	6,382,942.89		16%
6211	8,654,343.00	6,751,401.60	1,902,941.40		22%
6213	10,893,328.00	9,326,172.16	1,567,155.84		14%
6215	9,900,000.00	10,226,823.10		326,823.10	3%
6216	118,263,118.00	132,134,641.86		13,871,523.86	12%
6218	10,851,585.00	8,640,518.50	2,211,066.50		20%
6219	3,679,000.00	2,837,080.00	841,920.00		23%
6221	4,231,420.00	3,425,942.00	805,478.00		19%
6222	350,000.00	124,150.00	225,850.00		65%
6223	24,463,750.00	16,425,998.95	8,037,751.05		33%
6231	35,101,546.00	38,440,936.00		3,339,390.00	10%
6232	10,144,000.00	7,524,596.37	2,619,403.63		26%
6233	15,508,260.03	13,650,581.94	1,857,678.09		12%
6251	3,645,000.00	3,671,974.24		26,974.24	1%
6253	3,616,028.00	3,149,259.80	466,768.20		13%

6254	2,154,615.00	1,764,600.00	390,015.00		18%
6255	1,650,000.00	1,833,095.00		183,095.00	-11%
6256	483,300.00	665,998.79		182,698.79	-38%
6257	5,452,130.00	4,222,253.95	1,229,876.05		23%
6258	4,960,000.00	4,205,764.48	754,235.52		15%
6259	6,733,785.00	6,747,243.00		13,458.00	-0.2%
6271	9,200,000.00	7,715,253.71	1,484,746.29		16%
6412	2,065,000.00	2,069,500.00		(4,500.00)	-0.2%
6417	100,000.00	-	100,000.00		100%
			39,799,202.26	**26,480,819.98**	

<u>የካፒታል በጀት</u>

6314	38,207,283.00	47,557,135.79		9,349,852.79 (Supplier Advance Settlement)	24%
6315	150,000.00	-	150,000.00		100%
6322	87,070,000.00	63,461,283.33	23,608,716.67		27%
6323	154,254,339.56	128,544,232.37	25,710,107.19		17%
6324	127,930,475.33	130,378,934.45		2,448,459.12 (Advance Settlement)	-2%
6326	4,401,785.11	3,546,927.81	854,857.30		19%
6115	49,608,000.00	52,096,781.86		2,488,781.86	-5%
			50,323681.16	**14,287,093.77**	

ከውስጥ ገቢ

6114	30,000.00	32,400.00		2,400.00	-8%
6116	36,850,500.00	27,495,205.23	9,355,294.77		25%
6212	500,000.00	199,525.00	300,475.00		60%
6213	107,138.00	19,493.00	87,645.00		82%
6214	2,500,000.00	4,293,919.03		1,793,919.03	-72%
6215	150,000.00	-	150,000.00		100%
6217	578,000.00	187,791.23	390,208.77		68%
6218	107,000.00	-	107,000.00		100%
6219	69,000.00	39,560.00	29,440.00		43%
6231	5,690,262.00	3,451,621.08	2,238,640.92		39%
6232	510,000.00	398,501.32	111,498.68		22%
6233	680,824.94	515,704.79	165,120.15		24%
6241	10,000.00	6,350.00	3,650.00		37%
6252	572,175.03	430,600.00	141,575.03		25%
6253	340,250.00	153,640.00	186,610.00		55%
6313	2,926,500.00	-	2,926,500.00		100%
			16,193,658.32	**1,796,319.03**	

አባሪ 7 ተሽከርካሪን በተመለከተ

ተ.ቁ	የተሽከርካሪው አይነት	ታርጋ ቁጥር		ምርመራ
1	ሚትስቡሽ	4-14982 ኢ.ት	የነዳጅ ጌጅ የማይሰራ	የሚወገድ
2	ባጃጅ	4-0656 ኢ.ት	የነዳጅ ጌጅ የማይሰራ	ወጭ ለመቀነስ (ጥገና በተደጋጋሚ ስለሚፈልጉ)
3	ሞተር ሳይክል	4-0737 ኢ.ት	የነዳጅ ጌጅ የማይሰራ	ወጭ ለመቀነስ (ጥገና በተደጋጋሚ ስለሚፈልጉ)
4	ሞተር ሳይክል	4-0496 ኢ.ት	የነዳጅ ጌጅ የማይሰራ	ወጭ ለመቀነስ (ጥገና በተደጋጋሚ ስለሚፈልጉ)
5	ሞተር ሳይክል	4-0242 ኢ.ት	የነዳጅ ጌጅ የማይሰራ	ወጭ ለመቀነስ (ጥገና በተደጋጋሚ ስለሚፈልጉ)
6	ሞተር ሳይክል	4-0236 ኢ.ት	የነዳጅ ጌጅ የማይሰራ	ወጭ ለመቀነስ (ጥገና በተደጋጋሚ ስለሚፈልጉ)
7	ሞተር ሳይክል	4-0237 ኢ.ት	የነዳጅ ጌጅ የማይሰራ	ወጭ ለመቀነስ (ጥገና በተደጋጋሚ ስለሚፈልጉ)
8	ሞተር ሳይክል	4-0387 ኢ.ት	የነዳጅ ጌጅ የማይሰራ	ወጭ ለመቀነስ (ጥገና በተደጋጋሚ ስለሚፈልጉ)
9	ሞተር ሳይክል	4-0515 ኢ.ት	የነዳጅ ጌጅ የማይሰራ	ወጭ ለመቀነስ (ጥገና በተደጋጋሚ ስለሚፈልጉ)
10	ሃይሉክስ	3-48674 ኢ.ት	ኮድ 3 ታርጋ ተሽከርካሪ	ኮድ 4 ለማድረግ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡
11	ሃይሉክስ	3-48673 ኢ.ት	ኮድ 3 ታርጋ ተሽከርካሪ	ኮድ 4 ለማድረግ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡
12	ሃይሉክስ	3-84814 ኢ.ት	ኮድ 3 ታርጋ ተሽከርካሪ	ኮንትራክተሩ ሳያስረክብ ስለጠፋ በክስ ሂደት ላይ ነን
13	ሃይሉክስ	3-23309 ኢ.ት	ኮድ 3 ታርጋ ተሽከርካሪ	ኮንትራክተሩ ሳያስረክብ ስለጠፋ በክስ ሂደት ላይ ነን
14	ሃይሉክስ	3-44030 ኢ.ት	ኮድ 3 ታርጋ ተሽከርካሪ	ኮድ 4 ለማድረግ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡
15	ሃይሉክስ	3-42995 ኢ.ት	ኮድ 3 ታርጋ ተሽከርካሪ	ኮድ 4 ለማድረግ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡
16	ሃይሉክስ	3-32220 አአ	ኮድ 3 ታርጋ ተሽከርካሪ	ኮድ 4 ለማድረግ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡
17	ሃይሉክስ	3-19104 አአ	ኮድ 3 ታርጋ ተሽከርካሪ	ኮድ 4 ለማድረግ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡
18	ማርቸዲስ ባስ	4-12470 አአ	ኖርማላይዜሽን የማይሰራ	መኪናው ካምፓኒ ጥገና እየተደረገለት ነው
19	ሚትስቡሽ ፒካፕ	4-14852 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	ድሬዳዋ ኢንሹራንስ በጥገና ላይ ይገኛል
20	ሚኒባስ	4-14964 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	ግቢ ጋራጅ በጥገና ላይ ይገኛል፡፡
21	ኒሳን	4-14996 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	ግቢ ጋራጅ በጥገና ላይ ይገኛል፡፡
22	ኒሳን	4-14997 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	በስፔርፓርት እጥረት (ጎማ)
23	ሃይሉክስ	4-23358 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	ፓርኪንግ በቆመበት በስህተት የተመዘገበ
24	ኮብራ	4-12256 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	በስፔርፓርት እጥረት (ጎማ)
25	ሃይሉክስ	4-26329 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	የግለሰብ መኪና
26	ኒሳን	4-16531 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	በስፔርፓርት እጥረት (ፍሪሰዮን ሸራ)
27	ታታ ባስ	4-14961 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	በስፔርፓርት እጥረት (ሬለዘቤሪንግ)
28	ሚትስቡሽ ፒካፕ	4-14982 ኢ.ት	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	የሚወገድ በሞተር ችግር(በልሽት)
29	ሃይሉክስ	3-48674 አአ	የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው	ኮንትራክተሩ ሳያስረክብ ስለጠፋ በክስ ሂደት ላይ ነን
30	ሃይሉክስ	3-48673 አአ	የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው	ኮንትራክተሩ ሳያስረክብ ስለጠፋ በክስ ሂደት ላይ ነን
31	ሃይሉክስ	3-84814 አአ	የባለቤትነት መታወቂያ	ኮንትራክተሩ ሳያስረክብ ስለጠፋ በክስ

			ደብተር የሌላቸው	ሂደት ላይ ነን
32	ሃይሉክስ	3-23309 አአ	የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው	ኮንትራክተሩ ሳያስረክብ ስለጠፋ በክስ ሂደት ላይ ነን
33	ሞተር ሳይክል	4-0737	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	ፓርኪንግ በቆመበት በስህተት የተመዘገበ
34	ሞተር ሳይክል	4-0496	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	ፓርኪንግ በቆመበት በስህተት የተመዘገበ
35	ሞተር ሳይክል	4-0242	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	ፓርኪንግ በቆመበት በስህተት የተመዘገበ
36	ሞተር ሳይክል	4-0236	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	ፓርኪንግ በቆመበት በስህተት የተመዘገበ
37	ሞተር ሳይክል	4-0237	በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ	ፓርኪንግ በቆመበት በስህተት የተመዘገበ

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!